# በትንቢት የተገለጡ ክንዋኔዎች

ጀፈርሰንቪለ፥ ኢንዲያና USA

65-0801E

1 እስኪለጸሎት ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ። ጌታ ኣምላካችን፡ አንተ የሰማይንናየምድርን ታላቁ ፈጣሪ፡ ኢየሱስን ዳግም ከሙታን ኣውጥተህ፡ ለሁለት ሺህ ኣመታት ያክል፡ ቃሉን እያረጋገጠ እና በየትውልዱ ለሚገለጡህዝቦች የቃሉን እውነታነት እያረጋገጠ እንዲቆይ ያደረግከ። ኣሁን እየኖርንበት ያለውን ህይወት ካበቃ በኋላ፡ ሚመጣው ዓለም ዘለኣለማዊ ህይወት እንደምትሰጠን እያወቅን፡ ኣሁን በመካከላችን ስላለውመሎኮታዊው መገኘቱ እናመሰግንሃለን። ጌታ ሆይ ስለዚ ነገር እና የነፍሳችንን መልህቅ ስለሆነው ተስፋህ፣ ጽናትህን እና ደህንነትህንእናመሰግናለን። ማዕበሉ እና የሚሽከረከረውን ታላቁን ሞገድ ሲመጣም፡ በሱ ባለን እምነት ተደግፈን የትኛውም ማዕበል እንደምንገስጽ ይሰማናል።

ዛሬለደካሞች እና ለበሽተኖች ለመጸለይ በምንነሳበት ጊዜ ኣምላክ ይርዳን። ኣምላክ ሆይ ዛሬ ከዚ ስፍራ ስንሄድ በሽተኛ ሆኖ የሚመለስ እንዳይኖር እንጸልያለን። እዚህ ስፍራና እና በኣገሪቱ ወሰን ሁሉ ላይ በስልክ እጀታ ላሉ ሁሉ፡ ማንም በሽተኛ እንዳይገኝ፡በየህንጻው እና ህዝብ በተሰበበት ሁሉ እየሄድክ የደቀቁትን ሁሉ በመለኮታዊ ሃይል ፈውስልን። መንፈስህ ይፈውሳቸው። ታላቋ የጽድቅ ጸሃይ፡ ፈውስም በክንፎችዋ ይዛ፡ ቃልህን በሚሰሙ ልቦች ላይ የእምነትን ጨረር ታንጸባርቅባቸው፡ መንፈስ ቅዱስህ ኣሁንም ህያውእንደሆነ እንድያውቁ፡ የመንፈስቅዱስህ መገለጫዎችም ታሳይ። ኣባት ሆይ እነዚ በረከቶች በኢየሱስ ስም ጸለይን። ኣሜን።

አረፍበሉ።

2 ህዝቡንለ - ለመናገር እና ለበሽተኞች ለመጸለይ በዚ ስፍራ ስለተገኘን፡ እንደ ታላቅ መታደል እንቆጥረዋለን። በውጭ በምድሪቷ ሁሉ ላይሆነው በ - በቴለፎን መስመር ያሉትን ሁሉ ዛሬም እንደገና ሰላም እንድንላቸው እንወዳለን። እንዲሁም ደግሞ በዚ ማለዳ ክርስቶስንየተቀበላችሁ ሁሉ፡ መንፈስ ቅዱስ እንዲሞላችሁ እና በምድ ያለውን ሟች ህይወት እስኪያልቅ ድረስ ለሱ ታማኝ ሁናችሁ እያመንነው፡ ኣምላካችን ለእያንዳንዳችሁ እንዲባርካችሁእንጸልያለን። በሚመጣው ዘመን ፈጽመው ኣይሞቱም፡ ሁላችንም ለምንጠብቀው ታላቁ ዘመን።

3 ኣሁን እንዲህ እንላለን፡ ይሄን እያሰብኩ፡ ለማቋረጥ ፈልጌ ኣይደለም። ወንድማችንቨይል እዚ ኣለ፡ ምናልባት ላየው ባልችልም። እንዲህ ኣደርጋለው... ጽሁፉን ወደ ቱሰን ከተመለስኩ በኋላ ልላክልህ? ገና እያየሁት ነው፡ ሁሉንም ኣንብቤ ኣልጨረስኩም፡ ወደ ቱሳን እንደተመለስኩ እልክልሃለሁ።

አንድ ማስታወቅያ ለማድረግ እየፈለግኩ ነዉ። በተለይ ደግሞ በሁሉም ስፍራ ለሚገኙ አብያተ ክርስትያናት፡ በተለይ በምዕራብ ላሉ፣ ወይም መምጣት ለሚሻ ሁሉ። የተወደደ ወንድም፡ ወንድማችን ፔሪ ግሪን ... ስለ እነዚህ የተሌፎን መስመሮች በተመለከተ ጀማሪውእሱ ነው። ቱሰን መጥቶ እንዲጎበኘን እና በቱሰን ደግሞ ሪቫይቫል እንድናካሂድ ጌታ በልቡ ኣስቀመጠ፡ እኛም በጣም የምንፈልገው ነገርነው። ስለዚ ወንድማችን ፔሪ በቱሰን ይገኛል። ልታገኙት ከፈለጋችሁ እዛ ወደሚገኝ ቢሮአችን ጎራ በሉ። ነሐሴ 10፣ 11፣ 12 እንዲሁም 13 ድረስ ይሆናል። ለብዙ ያህል ጊዜ በልቡ ይዞት ነበረ፡ እኔም ኣልኩት “ከልብህ የምታስወግድበት ብቸኛው መንገድ፡ ሄደህ በማድረግ ነው” ኣልኩት። እውነተኛ የጌታ ባርያ ነው፡ ክርስትያን ወንድም ነው። እናንተም በቱሰን ያላቹ ህዝብ፡ ጌታ ባዘጋጀለት ስፍራ በሚያገለግልበት ስፍራ፡ ምናልባትም በራማዳ ኢንተርናሽናል ሊያገለግል ይችላል እና፡ እንደምትባረኩ ኣውቃለሁ። እዚህ እንዲያገለግል ኣልሆነለትም፡ይሁን እንጂ፡ የጌታን ቃል እንዴት እንደሚገላልጥልን፣ ለበሽተኖች ሲጸልይ እንዲሁም የጌታ ቅባት በሚሰራበት ሁሉ እንደምትባረኩ ኣውቃለሁ።

4 እንዲሁም ደግሞ ወንድማችን ኦርማን ነቪለን እና ወንድም ማንን፡ ከእናንተ ጋር ስለነበረን ቆንጆ የህብረት ጊዜ ልናመሰግናችሁ እንወዳለን። ከኦርማን ነቪለን እና ከወንድምማን የመሳሰሉ እንዲሁም እዚህ ያላችሁት ሌሎች ኣገልጋዮች ሁላችሁ ጋር ተባብሮ መስራቴ በጣም የሚያስደስት ነው። በእኛ የኣገልጋዮች ቦርድ ያልተጠቀሳችሁ ሰዎች ካላችሁ እርግጠኛ ነኝ ጌታ እንደ ባርያዎቹኣርጎ እውቅና ይሰጣቹኋል። ጌታ ለዘላለም ይባርካችሁ።

5 ባለፈው ምሽት ታማኞች እና ዲያቆናት ቦርድ ያደረጉት ስብሰባ በተመለከተ እኔ ... እንዳደርግ የተጠየቅኩባት ትንሽየ ጽሁፍ እኔጋ ኣለች፡ ቸርች ከመጀመሩ በፊት ደግሞ፡ እንደ ባህል ልንይዘው የተገባ እንደሆነተደርጎ በታማኞች እና በዲያቆናት ቦርድ ጸድቆ ተነቧል። በርግጥ በቤተክርስትያን ውስጥ በታማኞች እና በዲያቆናት ቦርድ የተደረገውውሳኔ፡ ሁሉንም ሊያስደስት ኣይችልም። ስለዚ ምንም ማድረግ ኣይቻልም። ከታማኞች እና ከዲያቆናት ቦርድ ጋር፡ እኔ የማደርገው ምንም ጉዳይ የለኝም። የተጣበበ ነገር ካልገጠመ በስተቀረ በነሱቦርድ ውስጥ ምንም ድምጽ መስጠት ኣልችልም፡ ሁለተኛው ድምጽ ደግሞወንድም ኦርማን ነቪለ ይወስዳል። ከዛ በኋላ እኛም የቤተክርስትያኑ ኣካል ስለሆንን፡ እንፈርምበታለን። እንዲሁም፡ የታማኞች ቦርድ በሚወስኑት የትኛውም የቦርድውሳኔ ውስጥ ኣንድ መቶ ፐርሰንት ሙሉ እንደግፋለን፡ ምክንያቱ ይሄን ለማድረግ የተሾሙ ስለሆኑ። ውሳኔዎቻቸው ደግሞ በእነሱ እናበጌታ መካከል ያለ ውሳኔ ነው። በምንም ይሁን ሁኔታ ውሳኔአቸውን ልጻረር ኣልችልም ኣላደርገውምም። ሌላ ተጨማሪም በዩናይትድ ስቴትስመንግስት በዚህ ኣይነት ውሳኔ ውስጥ እጄን እንዳላስገባ ተከልክያለው፡ ስለዚህ እባካችሁ ውሳኔአቸው እንዳርም ኣትጠይቁኝ። ላደርገው ኣልችልም፡ እንዲህ ኣይነቱ ነገርም ኣልሰማም። ኣያችሁ? ስለዚ ውሳኔአቸውን እንዳርም ኣትጠይቁኝ። ኣያችሁ፡ ያቦርድ፡ ቦርዱ ራሱ ነው ውሳኔውን የሚያሳልፈው። መልካም።

6 ሌላው፡በሚቀጥለው ስብሰባችን፡ የጌታ ፍቃድ ከሆነ፡ በአራት ወይም በስድስት ሳምንታት ኣከባቢ ለሌላ የእሁድ ስብሰባ ልመጣ እችል ይሆናል። በዚ ማለዳ ደግሞ በቃሉ ውስጥ የሚገለጥ ኣምላክ በሚል ርእስ ውስጥልናገር እንደሆነ አውጃለሁ፡ በርግጥ እውነት ለመናገር፡ ይሄን ለማድረግ የሚያችል በቂ ድምጽ የለኝም ዛሬ። የተሰበሰበውም ህዝብ፡በጭ ያለ የህዝ ብዛት በውስጥ እንዳለ የህዝብ ብዛት ያህል ነው። ባሶች እና ትልልቅ መኪኖችም እንዲሁ ከህዝቡ ጋር ብዙ

ቆሞዋል።ትንሿን ሞገድ ከፍተንም፡ ትንሽ ልንጨምር እንችላለን፡ ይሰማናል።እቺ ከዚህ ድንኳን (ጉባኤ) የምስራጭ ትንሿ ሞገድ፡ ኣጭር ሞገድ፡በየማይክሮፎኖቻችን መክፈት እንችላለን። እንዲሁም ዛሬ በቤተክርስትያኑ ዙርያ የተሰለፉት ብዙ መኪኖች የድምጽ ማጉያዎ ች ያላቸውናቸው። በቤተክርስትያን እንደዛረ ቀን፡ በውስጥም በውጭም እንዲህ ኣይነቱ የሰው ብዛት በግልጽ ኣጋጥሞን ያቃል ብየ ኣላምንም። ስለዚ ... ነን እንዲሁም ደግሞ ብዙ ብዙ ብዙ እየነዱ ያሉ ኣሉ።

ስለዚህም“ጥምብ ባለበት ኣሞራዎች ይሰባሰባሉ” የሚለውን ያሳየናል። ዛሬ ባለችው በዚህ ስብሰባ፡ ኣለም ኣቀፍ ስብሰባ ብየ ልጥራችሁን። ሁለትሶስተኛ የሚያህሉ የእስቴቶቹ ሕብረት ኣካላት ተወክለው እዚህ ተገኝተዋል፣ከሱም በላይ ደግሞ ኣምስት የውጭ ኣገራት፡ ሩስያም ሳትቀር፣ እንዲሁምደግሞ የተለያዩ የኣገሪቱ ክፍሎች።ከሩቅ ከቨንንዙዌላ እስከ ጀማይካ፣ ያገሪቱ የተለያዩ ክፍል የሚገኙብዙ ህዝብ፡ ኣምላክን ተርቦ እና ተጠምቶ እዚ ተገኝቶኣል። እንዴት ያለ ድንቅ ሰዐት ነው!

7 ኣሁን እንዲህ እፈልጋለው፡ መጽሓፍ ቅዱስ ከማንበባችን በፊት፡ ስለ'ኔ እንድትጸልዩልኝ እፈልጋለሁ። እንደ ጌታ ፈቃድ፡ የመሎኮታዊ ፈውስ ኣስፈላጊነትንበተመለከተ ትንሽ መልእክት ለማምምጣት እሞክ - እሞክራለው። በዚህ ማለዳ ስለመዳን በተመለከተ እናገራለው፡ ዛሬ ማታ ደግሞ መለኮታዊፈውስ ኣስመልክቼ ትንሽ ደቂቃ እናገር'ና ለህዝቡ ለመጸለይ የጸሎት ሰልፍን እንጠራለን። ያኔ እንዲህ በምናደርግበት ሰዓት፡ እንናተ በስልክ መስመር እያዳመጣችሁ ያላችሁ እና በየመኪኖቻችሁ ሆናችሁ ከቤተክርስትያኑሁለት ሶስት መታጥፊያ ዙርያ ያላችሁ ሁላችሁ፡ ለበሽተኞች ጸሎት በሚደረግ ሰዓት ወደ ህንጻው መግባት ካልቻላችሁ ... በርግጥምኣሁን ኣትችሉም፡ ምክንያቱ 'መተላለፍያዎቹ በሁሉ ኣቅጣጫ ተጣበዋል፡ የምታልፉበት ስፍራ መቀመጫ የትም ስለሌለ' ባላችሁበት ስፍራሁናችሁ እየጸለያችሁ ኣንዳችሁ ባንዳችሁ ላይ እጅ ጫኑ። የፈውስ ፕሮግራም በሚካሄድበ፡ የተገኛችሁ ኣገልጋዮችም ሁላችሁ ስለየጉባኤዎቻችሁጸልዩ። ጌታ በሁሉ ቦታ እንደሚገኝ እናምናለንና። ኣሁን ከማንበባችን በፊት፡ ወይም ...

8 ከመ- ከመጸለያችን በፊት፡ ከጌታ ቃል የተወሰነ ክፍል እናነባለን። ከትንሽ ጊዜም በፊት ቅዱስ ቃላቶቼን ለው - ለውጥ ኣድርጌኣለሁ፡ምክንያቱ ለዛሬ ማታ በኣእምሮየ ያዘጋጀሁትን የጉባኤው ኣይነት መቀየር ስለፈለግኩ፡ በተወሰነ መልኩ ለውጥ ኣድርጌበታለሁ፡ ቃላቱም መቀየር ነበረብኝ። እንድቀይራቸውሳይሆን፡ ህዝቡ፡ መለኮታዊ ፈውስን በተመለከተ በቀላሉ እንዲረዳው፡በሌላ ስርዓት ኣስቀምጨዋለሁ።

እስኪከቅዱስ ሉቃስ 24ተኛው ምዕራፍ እንክፈት። ከ ቁጥር 12 ጀምረንየጌታ ኢየሱስን ት ሳኤ በተመለከተ፡ እስከ ቁጥር 34 ድረስ እናነባለን።

ጴጥሮስ ግን ተነሥቶ ወደ መቃብር ሮጠ፤ በዚያም ዝቅ ብሎ ሲመለከት የተልባ እግር ልብስን ብቻ አየ፤ በሆነውም ነገር እየተደነቀ ወደ ቤቱ ሄደ።

እነሆም፥ ከእነርሱ ሁለቱ በዚያ ቀን ከኢየሩሳሌም ስድሳ ምዕራፍ ያህል ወደሚርቅ ኤማሁስ ወደሚባል መንደር ይሄዱ ነበር፤ [አንድ ማይል አስር ምዕራፍ ያህል ይሸፍናል፥ ስለዚ ስድስት ማይል ያህል ይርቃል።]

ስለዚህም ስለ ሆነው ነገር ሁሉ እርስ በርሳቸው ይነጋገሩ ነበር።

ሲነጋገሩና ሲመራመሩም፥ ኢየሱስ ራሱ ቀርቦ ከእነርሱ ጋር ይሄድ ነበር፤

ነገር ግን እንዳያውቁት ዓይናቸው ተይዞ ነበር።

እርሱም። እየጠወለጋችሁ ስትሄዱ፥ እርስ በርሳችሁ የምትነጋገሩአቸው እነዚህ ነገሮች ምንድር ናቸው? አላቸው።

ቀለዮጳ የሚባልም አንዱ መልሶ። አንተ በኢየሩሳሌም እንግዳ ሆነህ ለብቻህ ትኖራለህን? በእነዚህ ቀኖች በዚያ የሆነውን ነገር አታውቅምን? አለው።

እርሱም። ይህ ምንድር ነው? አላቸው።

9 [እንግዲህ አስቡት እራሱ ኢየሱስ ነው የሚያዋራቸው] እነርሱም እንዲህ አሉት። በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ሁሉ ፊት በሥራና በቃል ብርቱ ነቢይ ስለ ነበረው ስለ ናዝሬቱ ስለ ኢየሱስ፤

. . . እርሱንም የካህናት አለቆችና መኳንንቶቻችን ለሞት ፍርድ እንዴት አሳልፈው እንደ ሰጡትና እንደ ሰቀሉት ነው።

እኛ ግን እስራኤልን እንዲቤዥ ያለው እርሱ እንደ ሆነ ተስፋ አድርገን ነበር፤ ደግሞም ከዚህ ሁሉ ጋር ይህ ከሆነ ዛሬ ሦስተኛው ቀን ነው።

ደግሞም ከእኛ ውስጥ ማልደው ከመቃብሩ ዘንድ የነበሩት አንዳንድ ሴቶች አስገረሙን፤

ሥጋውንም ባጡ ጊዜ። ሕያው ነው የሚሉ የመላእክትን ራእይ ደግሞ አየን ሲሉ መጥተው ነበር።

ከእኛም ጋር ከነበሩት ወደ መቃብር ሄደው ሴቶች እንደ ተናገሩት ሆኖ አገኙት፥ እርሱን ግን አላዩትም።

10 [አድምጡኝ አሁን]

[ኢየሱስ] እርሱም። እናንተ የማታስተውሉ . . . ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማመን የዘገየ፤

ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና ወደ ክብሩ ይገባ ዘንድ ይገባው የለምን? አላቸው።

ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጐመላቸው።

ወደሚሄዱበትም መንደር ቀረቡ፥ እርሱም ሩቅ የሚሄድ መሰላቸው።

እነርሱ። ከእኛ ጋር እደር፥ ማታ ቀርቦአልና ቀኑም ሊመሽ ጀምሮአል ብለው ግድ አሉት፤ ከእነርሱም ጋር ሊያድር

ገባ።

ከእነርሱም ጋር በማዕድ ተቀምጦ ሳለ እንጀራውን አንሥቶ ባረከው፥ ቈርሶም ሰጣቸው፤

ዓይናቸውም ተከፈተ፥ አወቁትም፤ እርሱም ከእነርሱ ተሰወረ።

እርስ በርሳቸውም። በመንገድ ሲናገረን መጻሕፍትንም ሲከፍትልን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን? ተባባሉ።

በዚያችም ሰዓት ተነሥተው ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፥ አሥራ አንዱና ከእነርሱ ጋር የነበሩትም። ጌታ በእውነት ተነሥቶአል ለስምዖንም ታይቶአል እያሉ በአንድነት ተሰብስበው አገኙአቸው።

እነርሱም በመንገድ የሆነውን እንጀራውንም በቈረሰ ጊዜ እንዴት እንደ ታወቀላቸው ተረኩላቸው።

11 እንጸልይ። የተወደድክ ቸር ኣባት ሆይ፡ ስለቃልህ እናመሰግንሃለን፡ ቃልህ እውነት ነውና፡ ቃልህ ህይወት ነው። አንተና እና ጌታ ሆይ ቃልህአንድ ናቸው። እኛም እንጸልያለን፡ ጌታ ሆይ በትንሳኤህ ሃይል በእኛመካከል ትገለጥ ዘንድ፡ ዛሬም በዚቀ ትቀድመንም ዘንድ፡ እንደ ኤማሁስሰዎችም "ኪዛረበናን እተን ጽሑፋት ኪትርጉመልና ከሎዶ ግዳ ልብና ይነደና ኣይነበረን" እያልን ወደየ ቤቶቻችን እንድንመለስ እርዳን። ዛሬም እንደገና ማምሻው ሆኖኣልእና ጌታ ሆይ ኣድርግልን። ኣሜን ኣሜን።

12 እንግዲህኣሁን ስለዚህ መጽሓፍ መናገር እፈልጋለሁ። የዛሬ ርእሴ ደግሞ በትንቢት ግልጥ የደረጉ ኩነቶች የሚል ርእስ ነው። በትንቢት ግልጥየደረጉ ኩነቶች።

መጽሓፍቅዱስ ከሌሎች መንፈሳዊ መጻሕፍቶች የተለየ መጽሓፍ ነው። መጽሓፍ ቅዱስይለያል። ወደፊት ስለሚከናወኑ ነገሮችን የሚተነብይ፣ እንዲሁምደግሞ የ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት መገለጥን ያዘለ መጽሓፍ ነው። ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ድረስ ሙላቱን የሚያሳይ፡ እንዲሁም እንዴት እንደነበረ እና ምንእንደሆነ ያሳያል። ሙሉ መጽሓፉ ደግሞከምዕራፍ 1፡1 ጀምሮ እስከ 3 ድረስ፡ የኣምላክ ቃል የሆነውን "የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ" ይለዋል። "የኢየሱስ ክርስቶስ" የኣምላክቃል መገለጥ! (KJV ይመልከቱ)

13 ሌሎች መንፈሳዊ መጻሕፍቶች ሁሉ፡ የስነ ምግባር መዝገብ፣ ሞራላዊ እና ስነመለኮታዊ መዛግብት ብቻ ናቸው። የሆነ ... የመሓመዳውያን ቁርኣንእንዲሁም - እንዲሁም የቡድሂስቶች መጽሓፍ ስንቶቻችሁ ኣንብባቹሃል? ሰዎች እንዴት መኖር እንዳለባቸው፣ለምን መኖር እንዳለባቸውስነምግባር የሚያስተምሩ መዛግብቶች እንጂ፡ ትንቢት የላቸውም፣ ስለዚህ ነገር ስለ ተለየ ስጦታ ስለሚሰጠው፡ በኋላ ስለሚከናወነው ነገር የሚናገሩት ነገርየላቸውም። የሆነ ጎጆ ወይም ኣንድን ነገር እንደመቀላቀል ናቸው።ኣብያተ ክርስትያናትም፡ እንዲሁ ሄዳችሁ የምትቀላቀሉባቸው ጎጆዎች ሆነው ከተዘጋጁ፡ ከጌታ ቃል የራቁ ናቸው።

14 መጽሓፍቅዱስ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ህያው የሆነ ምስክር ነው። ምድር ወደሙላትዋ እንዳደገች ሁሉ፣ የወይን ሓረግም ወደ ሙላት እንደሚያድግ ሁሉ፣ ቀንም ወደ ሙላት ያድጋል፡ መጽሓፍ ቅዱስም ኢየሱስ ክርስቶስበሚባል ሰው ወደ ሙላት ያድጋል። እሱ የተገለጠ የኣምላክ ቃል ነው፡ ሙሉ የቤዛነት መጽሓፍ። መጽሓፍ ቅዱስ ለወደፊት የሚከናወኑነገሮችን የሚነግር ቃል ነው። ኣማኞቹም እንዲያነቡት እና በውስጡ የተጻፈውን ቃል በከፊል ብቻ ሳይሆን፡ በውስጡ የተጻፈውን ቃል ሁሉ እንዲያምኑ፡ በደራሲው ትእዛዝ ታዝዘዋል። ኣንዷን ቃል ኣለማመን፡-ምናልባትም እስከታምኗት ድረስ ሁሉን ነገር ልታቆሙ ትችላላችሁ። እያንዳንዱ ቃል ፍጹም የሆነ የሁሉ ቻዩን ኣምላክ ክፍል ነው። ኣምላክማንነቱን ለማሳየት ተገለጠ፡ ወደ ቃሉ ውስጥ ቆሰለ። እንደ ኣማኞች፡ እያንዳንዷን ቃል እንድናምን ትእዛዝ ታዝዘናል። በደራሲው በራሱ በኣምላካችንየተጻፈም ነው። ሊቀ ስበት ወይ ሊጨምርበት የሚችልማንም ሰው የለም።ብትጨምሩበት የኣምላክ ኣካል ኣስደንጋጭ ይሆን ነበረ። ምናልባትም በኣንድ እጅ ስድስት ጣት ወይም - ወይም ባለ ሶስት እጅ የመሳሰለ፣ከሱ ማጉደል ማለት ደግሞ ኣንድ እጅ ኣጭር ወይም ኣንዷ ጣት ኣጭር ይሆን ነበር። የኢየሱስ ክርስቶስ የኣካሉ ፍጹም ምልኣት ነው።በክርስቶስም እንደ ወንድ ሙሽራ ፡ ሙሽሪቱ እሱን የምትወክል ናት። እኚህ ሁለቱ ደግሞ ኣንድ ናቸው። " በዚያ ቀን፡ እኔ በአብ አብም በእኔ፣ እኔም በእናንተ እናንተም በእኔ እንደሆናችሁ ታውቃላችሁ።"እንዴት ያለ ግሩም ስዕል ነው!

እነዛ ቃሉን እንዳለ የተቀበሉት፣ ያመኑት እንዲሁም የተነገረላቸውንየተስፋውን ትንቢት በትዕግስት የሚጠባበቁ የቃሉ እውነተኛ ኣማኞቹም ሁሉ በዝያን ጊዜ ይገለጣሉ። እያንዳንዱ ኣማኝ ተግቶባታል። ተግቶ ሲጠብቅ የነበረውን እያንዳንዱ ኣማኝ፡ የተገለጠለት ነበረ።

15 ያኔ ጌታ ኢየሱስ በመጣበት ዘመን እስኪ ኣስታውሱ። መጽሓፍቅዱስ በኢሳያስ በግልጽ ስለ ዮሃንስ " የአዋጅ ነጋሪ ቃል - የጌታን መንገድ በምድረበዳ ጥረጉ፤ ለኣምላካችንም ጎዳና በበረሃ ኣስተካክሉ"ተብሎ ተጽፎ ሳለ ህዝቡ እንዴት ዮሃንስ ሊያውቁ ኣልቻሉም? የመጨረሻው ነብያቸው ማለት ሚልክያስ በምዕራፍ 3 ላይ፡ "እነሆ መልዕክተኛየንእልካለሁ፡ መንገድንም በፊተ ያስተካክላል።" ኣለ። ለምን ሊያዩትኣልቻሉም? ምክንያቱ ሃሳባቸው ሁሉ ከነሱ በፊት በተደረጉ ነገሮችላይ ጥለው ስለነበሩ ነው። የሃሳቦቻቸው መሰረት ሁሉ ከነሱ በፊት በተደረጉት መልዕክቶች መሰረት ያደረገ ስለነበረ። በሚኖሩበት ዘመን የነበረውን የጌታን የጊዜአቸው ኣሰራር ማየትንኣልቻሉም።

እናንተ በየትኛውም ስፍራ ያላችሁ ክርስትያኖች፡ ዛሬም ቢሆን የጌታ ቃል በእንዲህ መልኩ የቆመ ቃል ነው። ያለ ያለጥርጥር፡ እውነቱ ይህ ነው! በየትኛውም ስፍራ ያሉ ክርስትያኖች፡ ኣሁንም ቢሆን፡ አቶ ሉተር የጻፉት የስነ ባህርይ መዛግብትለማየት እንዲሁም ኣሁንም እንከን የማናወጣባቸውን የሚ/ር ዌስሊ፣ ሳንከይ፣ ፊነይ፣ ኖክስ፣ ካልቪን ጽሁፎች ለማገላበጥ ይሞክራሉ።ያግን ላለፈው ትውልድ ነበረ።

16 ፈሪሳውያንም ሙሴ ያላቸውን ለማየት ወደ ኋላቸው ተመልሰው እንዲህ ብለው ተናገሩ "እኛስ ሙሴአለልን። ኣንተ ግን ከወዴት መሆንህንም ኣናውቅም።" ኣሉ።

ነገር ግን ኣስታውሱ፡ ሙሴ ኣሁንም ቢመጣ ኖሮ ከወዴት መሆኑን ኣያውቁትም። ኣያችሁ? ኣሁን ደግሞ . . .

ኢየሱስ “እናንተ የነብያትን መቃብር የምታስጌጡ፡ የነብያትገዳዮች እናንተ ናችሁ” ቢላቸውም ኣያስደንቅም።መልእክቱ ይላካል፡ መልእክታቸው ካለፈ በኋላ! ህዝቡም ያዩታል፣ ይሳለቁበታል (ዓለምእንዲህ ነው)። ከዛ መልእክተኛውም ከጨረሰ በኋላ ምልዕክቱም ካበቃ በኋላ፡ መልዕክቱን መሰረት በማድረግ የሃይማኖት ድርጅቶችን ያቋቁሙበታል።ያን ጊዜ ሞት ይሞታሉ፡ ተመልሰውም ወደ ህይወት ኣይመጡም።

17 እስኪ ለትንሽ ጊዜ ኣስተውሉ፡ እዚ ላላችሁ ኣንዳንድ ሰዎችየምላችሁ ነገር ኣለኝ በተለይ ደግሞ እናንተ ካቶሊኮች ለእናንተ የምናገረው ኣለኝ። ትክክለኛውን የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስትያን ታሪክኣንብባችሁታል፡ ታውቁታላችሁን? ከሂፖኣዊው ቅዱስ ኣውጉስቲን ዘመን ጀምሮ ቤተክርስትያኒቱ ሚልዮኖች ንጹሃን ሰዎች ለሞት እንደዳረገች! በርግጥ ትክክለኛውን ቁጥር ብረሳውም፡ ከቅዱስ ሂፖ . .. ከሂፖው ቅዱስ ኣውጉስጢን . . . የሂፖው ዘመን ጀምሮ፡ ኣፍሪካ፡ሮማዊት ካቶሊክ ቤተክርስትያንን የሚቃወም የትኛውም ይሁን ሰው መሞትእንደሚገባ የሚል ግልጽ የሆነ ኣዋጅ ኣድርጋ ነበር። በመሆኑስ ቅዱስ ፓትሪክ እስከ ህልፈተ ህይወቱ በኋላ ድረስ፡ እንደ ሮማ ካቶሊክነቱ በፍጹም እውቅና ኣለማግኘቱንስ ታውቃላችሁ? ጳጳሱንእና ክፉቱን ሁሉ በመቃወሙ ምክንያት፡ ራስዋ ካቶሊክ ቤተክርስትያን በኣስር ሺዎች የሚቆጠሩ ልጆቹን ገደለች። እንዲሁም ደግሞ የኣርካዊትዋንዮኣንን ጠንቃይ ናት በማለት ራሷ ካቶሊክ ቤተክርስትያን በግንድ ላይኣስራ በእሳት እንዳቃጠለቻት ታውቃላችሁ? ከሁለት መቶ ኣመታት በኋላየቅዱሳንን ኣጽም ቆፍረው ኣወጡና፡ ትክክል ኣለመሆናቸውን ሲያውቁ፡ የሚቀበሩበት ቅዱስ ስፍራን እንኳ እንደሚገባቸው ኣላሰቡም ነገርግን ያለ ምንም ፍትሃት ወደ ባህር ጣልዋቸው።

ይህን ቀን ኣይለፋችሁ ሞኞች ኣትሁኑ።

18 ኢየሱስን የኮነኑት እነዛ ከሃናት በዚ ቀን እዚህ ለመምጣትእንዴት ይወዱ ነበር። ነገር ግን በጊዜው ያላዩ ትብቸኛው ነገር፡ የጊዜው ትንቢት ፈጽመው ኣለማየታቸው ነው። ቢያደርጉ . . . ኢየሱስ እንዲ ኣላቸው “ እናንተ በመጻሕፍት የዘላለምህይወት እንዳላችሁ፡ ይመስላቹኋል እና፡ እነርሱን ትመረምራላችሁ፡ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው።” ለዚያ ሰዓት።

ኣስተውሉ፡ መጽሓፍ ቅዱስ ፈጽሞ ኣይወድቅም። ኣንድ ነገር መሆን የማይችል ነገር ኣለ፡ የጌታ ቃል ኣይወድቅም፡ ምክንያቱ ደራሲው ከማድረጉ በፊት ኣስቀድሞ፡ የደራሲውን ስራዎችን ይዘረዝራልና።

19 ምናልባት ሰው እንዲህ ይሆናል ብሎ ቢገምት፡ የግምቱዕድል ምናልባት ከሺ ኣንድሊወጣለት ይችላል። የገመተውን ነገር የት እንደሚከናወን ከገመተ እማ የዕድሉ ውጤት ከኣስር ሺ ኣንድ ሊወጣለትይችል ይሆናል። ቀንዋን ከገመተ ደግሞ እድሉ ከሚልዮን ኣንድ ቢሆንነው። ግምቱ ማን እንደሚከሰት እማ ከሆነ ዕድሉ ከቢልዮኖች ኣንድ ይሆንበታል።

መጽሓፍ ቅዱስ ግን፡ በትክክል፡ ማን፣ መቼ፣ የት፣ ምን መጠበቅ እንዳለባችሁ ምንም ሳይሳሳት ይነግራቹኋል።ብዙም ኣልቆየም፡ እዚህ ኣከባቢ በሚገኘው ሳክርድ ሃርት ቸርች በተባለው ቤተክርስትያን ካህን ከሆነው ሰው ጋራ ኣነስ ያለች ንግግርተነጋግረን ነበር። ኣቶ ብራንሃም

“መጽሓፍ ቅዱስን ልትሟገት እየሞከርክ እኮነው” በማለት “ይሄ'ኮ የቤተክርስትያን ታሪክ ነው”ኣለኝ።

እኔም ኣልኩት “ይሄ ታሪክ ኣይደለም። ኣምላክ ራሱ በንድፉነው።” ኣልኩት።

“ኣምላክ እኮ በቤተክርስትያኑ ነው” ኣለኝ።

“ኣምላክ በቃሉ ነው። እሱን የሚጻረር ምንምይሁን ምን፡ውሸት ይሁን፡ እሱም ራሱ እንዳለ 'የሰውሁሉ ቃል ውሸት፡ የኔ ብቻግን እውነት ይሁን' ብሏልና።” ኣልኩት።

“ልንሟገት እኮ ኣይደለም።” ኣለኝ።

ታውቃለህ “እንሟገት ብየ ፍጹም ኣልጠየቅኩህም፡ መጽሓፍቅዱስ ራሱ ግን 'ኑና እንዋቀስ' ይላል” ኣልኩት።

20 ከመደረጉ በፊት፡ የደራሲውን ስራዎች ይተነብያል። እንግዲህይህን በመንገር፡ እያንዳንዱ ወንድ እና እያንዳንዷ ሴት ያለ ምንም ምህረት በፍርድ ወንበር ፊት ያስቀምጣል። ስለዚ ጉዳይ ሜተዲስቶችየሚሉት ከወሰዳችሁ፣ መጥምቃውያን የሚሉትን ከወሰዳችሁ፣ ካቶሊክ የሚሉትን፣ ጴንጤ ቆስጣሎች የሚሉትን ወይም የትኛውም ዓይነት ቸርችየምትለውም ከወሰዳችሁ፡ በፍርዳቸው ላይ ምናልባት ኣንዳንድ የሚያሳዝናችሁነገር ልታገኙባቸው ትችላላችሁ። መጽሓፍ ቅዱስ ግን ይሆናል የሚለውን ዝም ብላችሁ ብትጠብቁ፡ ይሆናል ያለውን ሲሆን ስታዩ ጊዜ፡መከናወኑን ትናገራላችሁ።

በርግጥ ኢየሱስ ራሱ፡ ከኣስተዋዮች እና ከጥበበኞች ዓይንሰውረህ፡ መማርን ለሚወዱ ህጻናት ስለገለጥህላቸው ኣመሰግንሃለው ብሎ ኣምላክን ስላመሰገነ፡ ሁሉንም ሰው በግልጽ ያየዋል ብሎ ማለት ኣይቻለም። ሁሉን ቻይ የሆነውን ኣምላክ በቃሉ ላይ ተቀምጦ፡ኣስተዋዮቹን እና ባለጸጋዎቹን እንዲሁም - እንዲሁም የተማሩ ኣዋቂዎችን ዓይኖች ኣሳውሮ፡ የድሆችን እና የመሃይሞችን ኣይኖች ሲከፍትኣስቡት።

21 እስኪ የኤማሁስን ሰዎችን ኣስቡኣቸው፡ ስለሱ የነበራቸው- የነበራቸውን ዕውቀት ትንሽ መሆኑን ነገራቸው። ቀኑን ሙሉ ኣብረዉት ሲያወሩ ውለው፡ ኣላወቁትም። እሱ ኣምላክ ስለሆነ፡ እንዲህም ይችላል።

ከሃናቶቹን እና ጸሃፍትን ያደረገባቸውም ይህንኑ ነው፡ እዲያደርግባቸው ተጽፎኣልና። እኛ እድል እንድናገኝ፡ ጌታ ኣይኖቻቸውን ኣሳወረ። ኣስተውሉ፡ የትኛውም የተማሩ ይሁኑ፣ እንደፈለጉም ካህን የነበሩ ይሁኑ፣ ብዙም ያደረጉትይኑር፣ ዕዉሮ ች ስለሆኑ ማየቱን ፈጽመው ኣይችሉም። ምናልባት የስጋ ኣይኖቻቸው ሀያ - በሀያ ሊሆኑ ይችላሉ፡ ቁምነገሩ መንፈሳዊ እይታ ነው!

22 በተመሳሳይ፡ በዛሬ ማለዳ ሴቶች ኣሁን እየለበሱት ባሉትኣለባበስ የሴት ኣመንዝራነትን በተመለከተ ልናገረው

እንደሞከርኩኝ ነው። ኣመንዝራዎች ናቸው። ወሲባዊ - መስህብ የተላበሰ ኣልባሳትስለሚለብሱ፡ በጌታ መጽሓፍ እይታ የምንዝርና ጥፋተኖች ናቸው። ነፍሳቸውእኮ ያለእውቀት ነው። ኣብዛኞቻቸው ሴቶች እኮ፡ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሴቶች እኮ ንጹሃን ናቸው፡ በየትኛውም ሁኔታ ስጋዊ ምንዝርና ያላደረጉ ሊሆኑ እንደሚችሉ ኣምናለሁ። ሚስኪን ሴቶች፡ ክፉ እንደሆነ እውነቱን የሚነግራቸውእያለ ነገር ግን ሳይገኝ በቀላሉ ያመነዝራሉ። መጽሓፍ ቅድስም እንዲህ ይላል “በብዙ ውሆች የተቀመጠችውን ጋለሞታ፡ የምድር ነገስታትእና በምድር ይሚኖሩ ሁሉ፣ ቸርቾችንና ሌሎች ሁሉ ከእርሷ ጋራ መንፈሳዊምንዝርና እንዳደረጉ። የጋለሞቶች እናት ።” የሃይማኖት ተቋማት።

23 ጌታ አምላክ በጨለማ እንደማይተወን፡ መጽሓፍ ቅዱሳችሁን ተመልከቱ።ነገሮች ከመከናወናቸው በፊት፡ ስለነገሮቹ ባህርያት እና ጊዜ እንዲተነብይልመጽሓፍ ቅዱስን ሰጠን።

ቀኑ ምን እንደሆነ ለማወቅ ካላንደርን እንደመመልከት ነው።ካሰባችሁ፡ ይህ እንዲህ ነው በሉ “ቅዳሜ ነው፣ እሁድነው፣ ምንድነው?” ቀን መቁጠሪያውን ተመልከቱ፡ ምን ቀን እንደሆነ፡ ቀን መቁጠሪያውን ይነግራቹኋል። የህዝቡን እንቅስቃሴስትመለከቱ፡ ምናልባት ወደ ቤተክርስትያን ሲሄዱ ስትመለከቱ፡ ወይም - ወይም ደግሞ . . . ደወል ሲደወል ስትሰሙ፡ ምንቀን ነውብላችሁ መደነቅ ትጀምራላችሁ። ካላንደሩን ተመልከቱት፡ ምን ቀን እንደሆነ ይነግራቹኋል።

24 እንዲሁም ደግሞ ቤተክርስትያን፡ በሰዶም ዘመን እንደነበረሁሉ ዓለማዊ እየሆነች እንደሆነች ስትመለከቱ፣ ዓለማዊትዋ ቤተክርስትያን ወደ . . . “የዚህን ክፉ ዘመን ኣምላክ” ኣምልኮ እየገባችእንደሆነች ኣስተውሉ፡ ይሄን ኣይታችሁ ስታበቁ፡ በኣምላክ መንፈስ መገለጥ ስር ሆነው፡ ሊሆን የተገባውን ቃል ተገልጦባቸው የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ህይወት እያሳዩየሚኖሩትን ጥቂቶችን ደግሞ ስትመለከቱ፡ በየትኛው ሰዓት እየኖራችሁእንደሆነ ማወቅ ትችላላችሁ።

ይህ መጽሓፍ፡ በትንቢት የሚናገረን በየትኛው ቀን እና ዘመን እየኖርን እንዳለን፣ በምንኖርበትምዘመን ውስጥ የሚከናወኑትን ክንውኖች ምንምን እንደሆኑ ይተነብይልናል። ሁሉ ጊዜም በየትኛውም ዐይነት ትውልድ ሳይሳሳት፡ እንደ ጽሁፎቹ ልክ ይተነብያል። እንዲያዩት ኣስቀድመው የተወሰኑት ሁሉ ስለሚያዩት፡ፈጽሞ ተሳስቶ ኣያውቅም እንዲሁም ወደፊት ኣይሳሳትም። ኢየሱስ ኣለ፡- “ኣብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም፡ እንዲሁም ኣባቴ የሰጠኝንን ሁሉ ይመጣሉ።” በቃ ቃል ከቅ ጋር እንደመያያዝ ነው። ሌላሊያደርግ ኣይችልም። እየኖርንባት ያለነውን ዘመን እናውቃታለን።

25 ነገር ግን በሁሉም ዘመናት እንደነበረ ሁሉ ሰዎች በቃሉላይየገዛ ራሳቸውን ትርጉም ይጨምሩበታል። በዚህም ምክንያት በዘመናቸው ውስጥ እየተከናወነ ያለውን ነገር እንዳያዩ ይታወራሉ። ፈሪሳውያንእና ሶዱቃውያን ተመሳሳይ ነገር። ጳውሎስ እንኳን ቆሞ ከቃል ጠቅሶ ሊናገር ሲሞክር፡ ሊቀ ካህኑን ነጭ ግድግዳ ብሎ ስለጠራው፡ አንድሰው ተነስቶ በጥፊ መታው። ስለዚህም ደግሞ ጌታ የተነበየውን ቃሉን ሲያረጋግጥ ማየት ተሳናቸው።

26 ኣስተውሉ፡ መጽሓፍ ቅዱስ ኣይጋጭም፡ መጽሓፍ ቅዱስ ኣምላክነው። በኣምላክም ውስት ግጭት ኣይኖርም፡ እርሱ ፍጹም ነው።

ነገር ግን ህዝቡ ከየራሱ ትርጉም ጋር! ወዳጆች ሆይ ኣሁንኣስተውሉ፡ ይሄን ላሳያችሁ፡ ኣብያተክርስትያናት ሁሉ በመጽሓፉ ትርጉም ላይ ሁሉም ኣይስማሙም። ሜተዲስቶች ከመጥምቃውያን፣ መጥምቃውያንከፕሪስቢተርያን ጋራ፣ ፕሪስቢተርያኖችም ከጴንጤ ቆስጣሎች ጋር ኣይስማሙም። እንዲሁም ደግሞ ኣርባዎቹ የጴንጤቆስጤ የተለያዩ ድርጅቶችም፡እርስ በእርስ ኣይግባቡም። ስለዚህም ኣያችሁ፡ እንደገና ባቢሎን መጣች፡ ኣለመግባባት።

ጌታ ግን የራሱ ቃል የሚተሮጉምበት የራሱመንገድ ኣለዉ።እንደሚያደርግ የተስፋቃል ይሰጥና እንዲሁም ራሱ ያደርገዋል። በዝያች ሰዓት ራሱን ስለሚገለጥባት የቃሉ ትርጉምም ራሱ ይሰጣል። የ- የክርስቶስ ኣካል ከእግር እስከ ራስ ድረስ ምን ያህል ርቃለች!

27 እንግዲህ እነዚህን ሰዎች ሊረዱት እንዴት እንዳልቻሉ ተመልከቱ፡ኢየሱስ እንዲያደርጉ እንደመከራቸው ቃሉን ከማንበብ ይልቅ፡ ሰው የነገራቸውን ነገሮችን ይሰማሉ። “እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩናቸው። እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ህይወት እንዳላችሁ፡ ይመስላቹኋል እና፡ እነርሱን ትመረምራላችሁ፡ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩናቸው።” በሌላ ኣባባል “ምን? ቃላቱን ኣንብቡ እና መሲሁ የሚያደርገውን ተመልከቱ። መሲሑ እንዴት ባለ ጊዜ እንደሚመጣም ተመልከቱ።መሲሑ እንደሚመጣ የሚያበስር ማን እንደሆነ ተመልከቱ፡ ሰዓቱን ተመልከቱ። በበረሀ የሚያውጅ የየውሃንስ ድምጽ። የወደዳችሁትን ኣደረጋችሁበት። ስመጣ ምንምን ማድረግ እንደሚገባኝ ተመልከቱ። ያደረጋችሁትስምንድነው? እኔይሄንን ሁሉ ማድረግ ኣቃተኝን?” ኣያችሁ፡ ኢየሱስ ሲናገር “ይሄንን ሁሉ ማድረግ ኣቃተኝን?”

28 እኛ ዛሬ ስለሱ የተነገሩ ትንቢቶች ሁሉ ሊከናወኑ በሚገባቸውመልኩ እንዴት በትክክል እንደተከናወኑ ቅዱስ ቃላቱን ኣገላብጠን ኣይተን እንዳወቅን ሁሉ፡ እነሱም እነዝህን ኩነቶቹን ሁሉ ማወቅይጠበቅባቸው ነበር። ለነሱ “ይሄ ሃይማኖት ኣልባ የሰላሳ ሶስት ዓመት ወይም . . . ሰላሳ ዓመትወጣት ተነስቶ ብርሃን ነኝ የሚል፡እርግብ የሚያርፍበት፡ እናም ስለምን . . . በቃ እንደ መዋረድ ነው።” እናም እንዲህ ኣሉት “ከድንግል ተወለድኩ የሚል የilligitimate ልጅ ነው” ኣሉት።

ኢሳያስ በትንቢተ ኢሳያስ 9፡6 ላይ “ህጻን ተወልዶልናል”ብሎ የተናገረውን ማወቅ ኣይጠበቅባቸውም ነበርን? ደግሞስ ነብዩ ኢሳያስ“ድንግል ትጸንሳለች” ብሎ የተናገረውስ ትንቢት ሊያውቁ ኣይገባምነበርን? እነኚህ ነገሮች ሁሉ ሊያውቁ ይገባቸው ነበር። ነገር ግን ኣስተውሉ፡ ችግራቸው ገና ወደፊት ይሆናል ብለው፡ ለወደፊት ስለተጠቀሙበትነው። እናም ደግሞ ይህ ሰው ለነሱ፡ መመዘኛዎ ቹ ሁሉ የማያሟላ ሰውነው። ነገር ግን እሱ እንዲህ ኣላቸው፡- “እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ህይወት እንዳላችሁ፡ ይመስላቹኋል እና፡ እነርሱን ትመረምራላችሁ፡እነርሱም ስለ እኔ መልዕክቶች የሚመሰክሩ ናቸው” ኣላቸው። ጌታ ያለው እንጂ፣ ቃሉ የተናገረው እንጂ፡ የስነመሎኮ ት ኣዋቂዎች

ያሉትኣይሆንም! አሜን!

ዛሬም ያውነው! መጻሕፍትን እንመርምር፡ ምክንያቱ እየኖርንበትየምንገኘውን ሰዓት እና በዚህ ጊዜ የሚከናወኑን ክንዋኔዎች ምንምን እንደሆኑ የሚነግሩን እነሱ ናቸውና። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመሰክሩትእነሱ ናቸውና፡ ልትደገፉባቸው የሚገቡት እነሱ ናቸው። ምክንያቱ መጽሓፉም ሲናገር "እሱ ትላንትናና ዛሬም እስከለዘለኣለም ያው ነው"ይላል። ምክንያቱ በዘመኑ የሚገለጥም መገለጥ እርሱ ስለሆነ። ሌላለውጥ ኣይፈጥርም።

29 ስለዚ፡ የሰዎችን ትርጉም በመስማታቸው፡ የጌታን ቃል ሲፈጸምማየት ፈለጉ፡ ነገር ግን ማየት ኣልቻሉም። እሱ ኩሉ ጊዜ ኣለ ነገር ግን እነሱ . . . ስለሚሰሙ . . . ኢየሱስም "የታወሩመሪዎች" ኣላቸው። ዕውር ዕውርን ቢመራ ምን ይሆናል? መጽሓፍ ቅዱስ ስለ መንፈሳዊ ስለሆነች የሎዶቅያ ዘመን ሲናገር፡ ዕውር እንደሆነችእንደተናገረ ኣስታውሱ። በዚ ዘመን እሱን በውጭ ኣርገውታል። ኢየሱስ ከቤተክርስትያን ውጪ የሆነባት ከዚች ከሎዶቅያ የቤተክርስትያንዘመን ሌላ የለም። በሎዶቅያ ግን በውጭ ሆኖ ውስጥ ለመግባት የሚፈልግበት ዘመን ናት። "እነሆ በደጅ ቆሜ ኣንኳኳለሁ" ይላል። እሱኮ በውስጥመሆን ነበር ያለበት። ነገር ግን እንዲህ ይላቸዋል "ሃብታምና ባለጠጋ ሆኜአለሁ ኣንድም ስንኳ ኣያስፈልገኝም የምትል ስለ ሆንህ፡ጎስቋላና ምስኪንም ድሀም ዕውር የሚመራህ ዕውር እና በመንፈስ ድሀ መሆንህን ኣታውቅም።" እንዴት ያለ ኣገ . . . አንድ ሰውበመንገድ ላይ ኣግኝታችሁት ምስኪን እና ዕውር ሆኖ ራቁቱ ካያችሁት፡ ራቁቱንም መሆኑን ነግራችሁት አንድን ነገር ማድረግ እንደሚችልኣውቃችሁ ብትነግሩት፡ የሆነ ነገር ያደርጋል። ነገር ግን ራሱን እያንቀሳቀሰ"ፈልጌው ነው። ምን ማድረግ እንዳለብኝ የምትነግረኝ አንተ ማነህ? የቆምሁበትን ኣውቃለሁ።" ቢል። እኔንጃ ይሄ እብደት ካልሆነኣላውቅም። የመጽሓፍ ቅዱስ ኣምላክ፡ በዝ ክፉ ዘመን ውስጥ፣ እኛ እየኖርንበት ባለነው የመጨረሻው የቤተክርስትያን ዘመን ላይ ቤተክርስትያንትገባበታለች ብሎ የተናገረውም ይህ ነው።

ስለህዝቡ ግን ኣስተውሉ "እኔ የምወዳቸውን ሁሉ እገስጻቸዋለሁ።" ይላል። እንግዲህ፡ ስለምታደርገው ነገርየጌታ ተግሳጽ ከደረሰህ፡ ካለህበት ተላቀቅ! ሽሽ። "እኔ የምወዳቸውንሁሉ እገስጻቸዋለሁ።"

30 እንግዲህ፡ ያኔ እነዛን ፈሪሳውያን፡ ኣምላክን በማየታቸው፡ እንዲህስ ቢሉ ኖሮ "ቆይቆይ ቆይ፡ ይህ ሰው የሚፈትነን ነገር ተናግሮናል፡ እንዲህም ብሎአል፡-እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ህይወት እንዳላችሁ፡ ይመስላቹኋልእና፡ እነርሱን ትመረምራላችሁ፡ እነርሱም ስለ እኔ መልዕክቶች የሚመሰክሩ ናቸው ብሎናል፡ እስኪ ሄጂ መጽሓፍን ልመርምር እርሱ ምንያደርግ ይሆን ልመልከት፣ እንዲሁም ማን እንደሆነ እና ማንን እንደሚወክል ልፈትሽ፡ ሄጂ ልመርምርን?" ቢሉ ኖሮ። ነገር ግን እንዲህከማድረግ ይልቅ፡ ወደ ከሃናቱ ይሄዱና ስለሱ ይጠይቃሉ። ልዩነቱን ኣያችሁ? ቃሉን ማንበብ ነበረባቸው።

31 መጽሓፍ ቅዱስ በዕብራውያን 1፡1 "ኣምላክ ከጥንት ጀምሮ በብዙ ዓይነት እና በብዙ ጎዳና መጽሓፍ ቅዱስን በነብያትጻፈ።" ኣስተውሉ፡ መጽሓፍ ቅዱስን ሲጽፍ በራሱ በመረጠው መንገድ ነው። ኣያችሁ? በእንዲህ መልኩ እንዲጽፈው ግዴታው ኣይደለም።የሰውንስ ልጅ በደም ማዳን ኣለበትን። ወንጌል ግዴታ በሰው መስበክ ኣይጠበቅበትም። ቢያስፈልገው ወንጌሉ እንዲሰብኩለት፡ ጸሓይን፣ ጨረቃን ከዋክብትን ማድረግ ይችላል፡ እንዲሁም፡ ንፋሳትን ወንጌልንእንዲሰብኩ ሽውው ማድረግ ይችላል። እሱ ግን ሰውን መረጠ! ቃሉ የመጣበትን ኣመጣጥ መረጠ፡ እሱም ከጥንት የኣካሉ ክፍል ሆነው ከጥንትየተወሰኑ እና ኣስቀድመው የተሾሙ ነብያቶች ስለነበሩ፡ ለሚኖሩባትዘመን እና ትውልድ የቃሉን መገለጥ ኣወጁ። ምክንያቱ "የጌታ ቃል ወደ ነብያት ብቻ ስለሚመጣ።" የስነ መለኮት ኣዋቂዎች ወደሆኑት ኣይመጣም። ቃሉን ኣሳዩኝ። ወደ ነብያት ብቻ ነው የሚመጣው። ጌታ ኣይዋሽም። ስለዚ ጌታ መጽሓፉን በመረጠው መንገድእና በመረጣቸው ነብያቶቹ ጻፈ። ሰዎች የመረጡዋቸው ነብያቶች ሳይሆኑ ጌታ በመረጣቸው ነብያት።

32 ኣማኖቹም፡ ነብያቶቻቸው ያልዋቸውን ነገር እስኪፈጸም ድረስይጠባበቃሉ፡ እውነተኛ የኣምላክ ነብያት መሆናቸውን የሚታወቁበትም ነው። ምክንያቱ ነብያት በመጀመርያ በመንፈስ የተደገፉ ናቸው፣ሁለተኛ ደግሞ ሁልጊዜ በዘመኑ ቃል ላይ ይጸናሉ። መተማመኛው ይህነው። ባለፈው እሁድ ብዙ ሓሰተኛ ነብያቶች እንደሚነሱ የተማርነውን ኣስቡ። እንዲሁም በልዓም እና ሙሴ በተመሳሳይ መንፈስ የተቀቡነብያት መኖራቸውን ደግሞ እንደ ምሳሌ ኣይተናቸዋል። ከሁለቱ አንዱ ግን እንዲህ ኣለ ፦ "ሁላችንም እኮ አንድ ነን። ሴቶቻችንንእና እኛ ሁላችን በህብረት እንሁን። ቆንጆ ኮረዳዎች ኣሉን እናንተም ወንዶች ወዲህ ቅረቡ ለራሳችሁም ቆንጆ ሚስት ውሰዱ፡ ችግር የለም፡ አንድ ህዝብ ነን፡ ያውም አንድ ዘር ነን።"ህዝቡም ይሄንን ነገር ተቀብለው ነበርና፡ ጌታ በፍጹም ስለዚህ ነገራቸው ኣልማራቸውም።

ኣስተውሉ፡ ዓለም እና ህዝ - ህዝብ ሁሉ ቆረጣን ይፈልጋሉ፣ ቀላል መተላለፍያ፣ ኣቋራጭንይፈልጋሉ። በጌታ ቃል ግን ኣቋራጭ ብሎ ነገር የለም። አንድ መንገድ ተዘጋጅታለች፡ ሰውነታችን በዛች መንገድ ልክ እንከርክም እንጂ፡መንገዱን በኛ ልክ ለማድረግ ኣንከርክም። ሁሉም ሰው እንዲህ ማድረግ ይጠበቅበታል። ኣምላክ የሚሰራበት ብቸኛው መንገድ ይህ ነው።

33 ኣያችሁ፡ በሰው ኣልተጻፈም፡ በጌታ ኣምላክ ነው የተጻፈው፡ የሰው መጽሓፍ ኣይደለም። ስለዚህ ደግሞ ኣማኞች የቃሉ ማረጋገጫ እስኪያገኙ ድረስ ይጠባበቃሉ።

አንድ ሰው እንዲህ ኣለ፡- "እንዲሁ የቆየ የእብራይስጥ ጽሁፍነው" ኣለ። ዕብራውያን የገዛ ራሳቸውን የሚኰንን ጽሁፍ ይጽፉሉን? እንዲህ ዐይነትዋ የኣይሁድ ኣገር፡ በግሏ - እስታይል ያለችየጸዳች የኣይሁድ ኣገር፡ የራሳቸውን ዐመጽ በመጻፍ ራሳቸውን ይኮኑናሉን? በፍጹም ኣያደርጉትም። ሓጢአታቸውን ሊናገሩ፣ ወደ ጣኦታትእንዴት እንደሄዱ፣ በጌታ ቃል ላይ እንዴት ኣምጸው ዘማዊ እንደሆኑ ሊናገሩ? ኣይ በጭራሽ፡ ያቺ ኩሩ ኣገር፡ እንዲህ ኣታደርግም።

የሰው መጽሓፍ ኣይደለም። የኣምላክ መጽሓፍ ነው። ብዙ ጊዜደግሞ ራእዮች የሚያይና የኣምላክን ድምጽ የሚሰማ ሰው በኣብዛኛው ፍጹም ኣይረዳውም (ብዙ ጊዜ።) ኣያችሁ? መጽሓፍ ቅዱስ ሰው ኣልጻፈውም፡ጌታ ነው

የጻፈው። የሰው - የሰው መጽሐፍ አይደለም፣ የአምላክ መጽሐፍ ነው። በሰው አንደበት የተተረከ የአምላክ ሐሳብ ነው። መጽሐፍቅዱስያስባለውም ይህ ነው። ቃል ማለት የተተረከ ሐሳብ ማለት ነው። በመጀመርያም የአምላክ ሐሳብ ነበረ፡ ሐሳቡም በነብያቶቹ አንደበትተረኮ በኣገልጋዮቹ ኣረጋገጠው። ኣያችሁ? ኣስተውሉ።

34 ኣምላክ የራሱ ኣመራረጥ ኣለው፡ ለእያንዳንዱ ትውልድ የመረጣቸውነብያት ኣስቀድሞ በወሰነው ሃሳቡ ነው። ነብዪው ከትውልዱ ሁኔታዎችን እንዲስማማ ኣድርጎ ያዘጋጀዋል። ኣያችሁ፡ ያደረገውን ያድርግከልኩ ኣያልፍም። የተማረም ይሁን ያልተማረ እንዲስማማ ያደርገዋል። ስጦታዎቹን ያበጅለታል፡ የሚሰብከበትን ኣኳኋን፣ የሚኖረው ስጦታዎች ሁሉ ልክ ያደርግለታል። ለዛች ትውልድ የሚሆን ምልእክትም ጭምር፣ ጌታ ኣንዳችነገር እንድትከናወን በወሰነባት ስፍራ፡ ስፍራውን ሊወስድ የሚችል ምንም ነገር ኣይኖርም። ምንም ይሁን፡ የትኛውም ሰው - ሰራሽውጤቶች ይሁኑ፡ ስፍራውን ሊወስድ ማንም ኣይችልም። ምናልባትም ሰውየውን መሃይም ኣድርጎ ወስኖት ሊሆን ይችላል፣ ወይም ምናልባትምሌላ ዐይነት ሰው ኣርጎ ወስኖት ይሆናል። ምንም ይሁን ምን የራሱ ስፍራ ይሰጠዋል፣ የ - የ የራሱ ስጦታ፣ የራሱ ተፈጥሮ፣ የራሱስልት፣ የሆነ ይሁን፡ ራሱን የሚገልጥበት መንገድ፣ የሚያደርገው ሁሉ። የጊዜው ሰዎችን ማጥመድ የሚችል የጊዜውን ሰው ያደርገዋል።ኣዎ፡ እንዲህ ኣድርጎታል።

ሁልጊዜም በያንዳንዱ ዘመን መጨረሻ፡ ቤተክርስትያን በዐለማዊነት እና በሓጢኣትተወስዳ፡ በሰው የተሳሳተ ትርጉም በተሰጠው የቃል ትርጉም ስትደገፍ፡ እንደዱሮኣቸው በዘመኑ መጨረሻ ላይ ፈጽሞ እስኪረባበሽ ድረስ፡በስነ - መሎኮታውያን እና በከሃናት መበላሸት ይጀምራል። ትርጉሞቻቸው ሁልጊዜ ስሕተት ነው፡ ስሕተት ያልሆነበት ጊዜ ኣልነበረም። የጌታ ቃልም ትክክል ያልሆነበት ጊዜ ፍጹም ኣልነበረም። ልዩነቱም ይህ ነው።

35 ስለዚ ኣያችሁ፡ መጽሐፍ ቅዱስን የጻፈው ኣምላክ እራሱ ነው። ጌታ፥ የሚናገር ኣምላክ ነው። ሙሴንንም እንደተናገረው ይገልጻል። ኤርሚያስም "በኣፌ ውስጥ ቃሉን ኣኖረ" ይላል። መጻፍም ይችላል፡ ኣስርቱ ትእዛዛት በራሱ ጣት ጻፋቸው። በባቢሎን ግንብም እንዲሁጻፈ። ሌላም፡ በብሉይ ኪዳን ላይ ብቻ፡ ነብያት ሁሉ ሁለት ሺህ ጊዜ "ጌታሰራዊት እንዲህ ይላል!" ማለታቸውን ኣስታውሱ። በርግጠኝነት ኣምላክ ይናገራል፣ ኣምላግ መጻፍ ይችላል። ዘጠና ፐርሰንት ያክልየማቴዎስ፣ የማርቆስ፣ የሉቃስ፣ እና ዮሃንስ ቃላት የኣምላክ የራሱ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ናቸው። እንግዲህ ኣምላክ የሚጽፍከሆነ፣ ኣምላክ የሚያነብ ከሆነ፣ የሚናገርም ከሆነ፡ ሌሎችን እንዲህ እንዲያደርጉ ማድረግ ይሳነዋልን? ሙሴን፡- "ሰውን ዲዳ ያደረገ፣እንዲናገርስ የሰጠ ማነው?" ኣለው። ጌታ እንደ ራሱ ኣሰራር፡ መጽሐፍ ቅዱስን በነብያት ጻፈው።

36 በየጊዜው ቤተክርስትያን ነገሮች በሚቀላቀልባት ወቅት፡ ጌታየተስፋ ቃል እንደሰጠ፡ ለትውልዱ የሚሆን በቃል መገለጥ እና በምልክቶች ድንቆች የተረጋገጠ "ቃሉን ምልክቶችን በማስከተል የሚያረጋግጥ"የተዘጋጀ ነብዪ ኣለው (እርሱ ሁሉን የሚያውቅ ኣምላክ ስለሆነ፡ እንደምትበላሽም ያውቃል።) በነብዪው በስተጀርባ በመሆን፡ ስለራሱ ትክክለኛ ትርጉም ይሰጣል።

እሱ - ለእነሱ - ከተላከላቸው ምርጦቹ በስተቀር፡ በሌሎች በሁሉም የተጠላ ይሆናል። ይሄን ትክክል ነው ሃሰት ለማወቅ፡ እያንዳንዷ ሂደት መርምሩ። እነዚያ የተላከላቸውን ብቻ! "ወደ ገዛ ወገኖቹ መጣ፡ የገዛ ወገኖቹም ኣልተቀበሉትም፡ለተቀበሉት ግን በስሙ ለሚያምኑ፣ የኣምላክ ልጆች ይሆኑ ዘንድ ስልጣንን ሰጣቸው።" ብዙ ጊዜ እንደሰበክኩት፡ በሁሉም ኣጋጣሚዎች፣በየዘመናቱ የፍጻሜ ጠርዝ እና መገናኛ . . . በሁሉ የቃሉ ምርመራኣስተውሉ።

37 እስኪ የኖህን ዘመን ተመልከቱት፡ የፍርድ ጠርዝ ከመድረሱበፊት፡ ምን ነበር የሆነው? ኖህ፡ የገዛ ቤተሰቦቹ ብቻ ነበር ያመኑት። ሌሎቹ ሁሉ ግን ነቀፉት። መላ ዐለምም እንዲሁ ጠፉች።

በአብርሀም ዘመንስ! ከአብርሀም ወገን የሆኑቱ ብቻ ያመኑት።መልኣኩ ሶዶም ወርዶ በሰበከ ጊዜ፡ ሎጥ እና ሚስቱ ሁለቱም ልጆቹ ብቻ ወጡ፣ ወደኋላ የተመለከተችውን፡ የጨው ዐምድ ሆና ቀረች።

በሙሴስ ዘመን፡ የተመረጠው እስራኤል ብቻውን ወጣ። ፈርኦንደግሞ ጠላው።

በኤልያስስ ዘመን! ከሰባት ሺው ህዝብ ውጪ፡ (በቃ በጠቅላላበሚባል ደረጃ) ሁሉም ጠሉት። ምድሪቷ በሙሉ።

በኤርሚያስ ዘመንስ? ለብዙ ቀናትበኣንደኛው ጎኑ ስለተኛ እንዲሁም በሌላኛው ጎኑ እየተኛ - ምልክቶችን ስለተጠቀመ፡ ያልበሰለ ፍራፍሬ እየወረወሩበት ለምን እብድ ኣሉት?። በቃ ጠሉት።

ኢሳያስ በመቁረጫ ለሁለት እስኪሰነጥቁት ድረስ፥ ትውልዱን በሃይል ገሰጻቸው።

38 እንዲሁም መጥምቁ ዮሃንስ "በምድረበዳ የሚኖር፡ የሚጮህእብድ።" እንደ ቸርች! ወደ - ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቀረቡት ደቀ መዛሙርት ውጪ ሁሉ ተቃወመው።ይሄውላችሁ እንግዲህ። ዮሃንስ ህዝብን ኣዘጋጀ። ስንት ሰው ነበሩት? በሁለቱም የእጆቻችሁ ጣቶች . . . የሚቆጠሩ ነበሩ። ኢየሱስበመጣ ጊዜ፡ ዮሃንስ ወደ እርሱ ያቀረባቸው ሰዎች ስንት ያህሉ ነበር? ኣስቡት እስኪ! በዳግም መምጣቱስጊዜ?

ይሁን እንጂ ትክክለኞቹ የመጽሃፍ ቅዱስ ኣማኞች፡ በዘመናቸው የተገለጠውን የጌታ ቃል በግልጽ ሲያዩ፡ ወድያው ያምናሉ። በምንም መልኩ ከማመን ልታግዱኣቸውኣይቻልም። ሌላው ይቅር ምስክርነታቸው በደማቸው እስከ ማተም ድረስ ያምናሉ። የተወሰነውን ዘመን ማየትን እና ማመንን ደግሞ ለነሱ፡ ኣስቀድመው ለተወሰኑቱ ነው።

39 ሌሎቻቸው ማየትን ኣይችሉም። ታውረዋል። እንግዲህ "ማየትንኣይችሉም ብለናል።" ለምሳሌ እንደነ በልዓም የመሳሰሉት፡- በልዓም 'ኮ የተቀባ ነብዪ ነበረ፡ ታድያ እንዴት ሊገባው ኣልቻለም? ፈርኦንስ!የጌታ እጅ ተገልጣ በፊቱ ተኣምራቶችን እና ድንቆችን ስትሰራ፡ እንዴት ማየት ኣቃተው? ጭራሽ ልቡን ኣደነደነበት። እውነት ነው ኣይደል? ዳታንስ! ኣይሁዳዊ ሆኖ እንዴት ይሄንን ማየት ተሳነው? በተከፈለውባህር ተሻግሮ፣ በየምሽቱ የሚወርደውን ፍሬሽ መና እየተመገበ፣ ማየትን ግን ኣልቻለም። ቆራሕስ እንዴት ኣላየም? ቀያፋስ! በዘመኑለነበሩ የሓይማኖት ሰዎች ራስ ሆኖ ሳለ፡ እንዴት ይሄንን ማየት ኣቃተው?መሲሑን መለየት እንዴት ተሳነው? ይሁዳስ እንዴት ታወረ? ይሁዳ'ኮ ኣብሯቸው

ነበረ፣ ኣብሮም ተጓዘ፣ ተኣምራቶችንም ኣደረገ። ይሁንእንጂ ቃሉ ይፈጸም ዘንድ የግድ ኣለው። መጽሓፍ እንደሚል፡ ለዚህ ኣስነሳሁህ ነው። ለዚሁ ዓላማ የተፈጠሩ ናቸው። ይህ እውነት ነው።ሮሜ 8 ይላልና።

40 እንግዲህ ኣማኞች፡ ኣምላክ የተናገረው ቃል ስጋ ሲለብስበየትውልዳቸው ማየት ይችላሉ። እነዛ እውነተኖች ሰባት ሺህ ሰዎች (ሰባት መቶ ሰዎች ናቸው?) በኤልያስ ዘመን። ሰባት ሺህ ሰውነበሩ እንጂ። በኤልያስ ዘመን ላይ ከሁለት ከሶስት ሚልዮን ህዝብ ውስጥ፡ ትክክለኛውን ማየት የቻሉ ሰባት ሺህ ሰዎች ብቻ ነበሩ።እምብዛም፡ ኣንድ መቶኛ ኣይሆኑም። ያዩ ት ነገር ግን እውነት ነበረ፣የኣምላክን መገለጥ ኣዩ። ያቺ ኤልሳዕ ወደ እርሷ የተላከባት መበለትስ፡ ለርሷእና ለልጅዋ የሚሆን ቂጣ ጋግራ፡ እሷን በልተው ለመሞት ኣስባ ነበር። ኤልያስን ግን ያለው ኣስተውሉ “ የሰራዊት ጌታ እንዲህ ይላል፡ጌታ ወደ ምድር ዝናብ እስኪልክ ድረስ፡ ከማድጋሽ ዱቄት ከማሰሮሽምዘይት ኣይደርቅም እና፣ መጀመርያ ለኔ ጋግረሽ ኣምጪልኝ” ኣላት። ሳታንገራግር፡ ሄዳ ጋግራ ሰጠችው። “መጀመርያ ለኔ ከዛም ላንቺእና ለልጅሽ ኣንድ ጋግሪ” ብሏት ነበር። ኣስቀድማም የተወሰነች ዘር ስለነበረች ሰውየውን ሰማቺው እንዲሁም ኣየችው።

41 ኣብዛኞቹ ስለሱ “እዩት ይሄ እብድ ሽማግሌ። ኣምላክ በሱምክንያት ረግሞናል” ኣወቃችሁት፣ ኢልያስን “እስራኤልን የምትገለባብጥ ኣንተ ነህ” ሲባባሉበት ነበርና።

እሱ ግን ኣላቸው “እስራኤል የምትገለባብጡ እናንተ ናችሁ”ኣለ። ኣያችሁ የአምላክ . . . የማን ቃል ነበረ የሚያበራው? ቃሉ ነበር።

መጽሓፍ ቅዱስ ስለ የማያምንቱ ሲናገር . . . ለዚሁ ዓላማ እንደተፈጠሩ ይናገራል። ነገር ግን እውነተኛ ኣማኞች የሆኑቱ በዘመኑ የተገለጠውንቃል ስጋ ሲሆን ስያዩ፣ ኣምላክ በሰው ኣንደበት ሲናገር፣ እንዲህ ኣደርጋለሁ ያለውን ካደረገ፡ ይሄንን ሁሉ ይመልሰዋል!

42 እንግዲህ ምልክቶችን ኣትመልከቱ። ሌላውን እዩ። በምልክቶችከተወሰዳችሁ፣ እንደተቀረው ዓለም ትሞኛላችሁ። የሚቻል ቢሆን ኖሮስ የተመረጡት ለማሳት፣ ሃሰተኛ ነብያት ይነሳሉ፡ ድንቆችንም ምልክቶችንምያሳያሉ። ቃሉን ያዙ። ካሃናቶችን እና ነብያቶቹን እዩዋቸው፣ የእብራውያን ነብያት። ሰደቅያስ እስከነ ሁለት ታላላቅ ቀንዶቹ “በአምላክ-የተቀባሁ ነብዪ ነኝ።” ኣዎ “መንፈስቅዱስ የወረደባቸው፣ ያቺ ምድር የኛ መሆንዋን በአንድነት የሚያረጋግጡ ሶስት መቶ ዘጠናዘጠኝ ነብያት ከነ ጋራ ኣሉ። እንሂድ እና እንውጣባት። ኣክዓብ ሆይ በምድራችን ያሉትን ጠላቶቻችን በእነዚህ ቀንዶች ትወጋቸዋለህና፡ጌታ የሰጠን ምድር ሄደን እንውረሳት።”

43 ኢዮሳፍጥ የተባለውን፡ ሃይማኖታዊው መልካም ሰው ያለውን ኣስተውሉ “ሌላ የለህምን?”

“ሌላ? ይሄው አራት መቶ በአንድነት ተስማምተዋል!” ኣለው።“አንድ አለ ይሁን እንጂ አልወደውም።” “ድምጹን ከፍ ኣድርጎ ይገስጸናል፡ ምን ያህል ሓጢያተኖች መሆናችንን ይናገራል” “እኔ እጠላዋለሁ!እሱም የይምላ ልጅ ሚኪያስ ነው።”

ኢዮሳፍጥም “ንጉስ እንዲህ ኣይበል። እሱ ይምጣ እና የሚለውንደግሞ እንስማ።” ኣለው።

ሄደውም ባመጡት ጊዜ “ጊዜ ስጡኝ ጌታ የሚለውምን እንደሆነ ልይ።” ኣላቸው

አክዓብም “ከእውነት ሌላ እንዳትዋሸኝ ኣምልሃለሁ” ኣለው።

ሰውየው መጥቶ “እንግዲህ በመልካም መመለስ ከፈለግክ፡ ሌሎቹእንዳሉት በል ብሎት ነበር።”

ሚኪያስም “ጌታ የሚናገረውን እናገራለሁ።” ኣለ። ኣያችሁ?

በሚቀጥለውም ቀን፡ ነገስታቱልብሰ መንግስታቸውን ለብሰው በደጅ ተቀምጠው፡ እንዲሁም ታዋቂ ሰዎች ሁሉ ተሰብስበው፦ ነብያቶቹም እዛ ቆሞው ሳሉ “አንተ እብዱ፡ ስለዚ ጉዳይ ምንትላለህ?”

ኣላቸውም “ሂድ ተከናወን።” “እስራኤል ሁሉ ያለ እረኛእንዳሉ በጎች ተበታትነው ኣየሁ” ኣላቸው።

44 መጣና መታው . . . እጁን ኣንስቶ ኣፉን መታው። ነብዪውነብዪን ኣፍ መታ። ኣራት መቶ ነብያት ሁሉ፡ በአንዱ ላይ ተነስተው ይተነብያሉ፣ በርግጥ ከበድ ያለ ነገር ይመስላል። ኣያችሁ ሁልጊዜየብዙሃኑ ምክር ባለበት ስፍራ ሁሉ፡ ደህንነት የለም። ያሉበትን ስፍራ በመመርኮዝ . . . የሚመክሩትን ምክር ምንነት፣ ምክሩስለምንድነ በሚል ምርኮዛ ውስጥ ለንጉሱ የሚቀርለት ደህንነት ኣልነበረም፡ የብዙሃኑም ምክር እንደ እውነት ወሰደ። ቆም ቢል ኖሮ፣ኤልያስም የተናገረውን ለማወቅ ጥቅልሉን ቢከፍት ኖሮ።

45 ሚኪያስም ኣፉን ባልከፈተ ነበር። አላወቀም፣ ምናልባትም ጌታ፡ ለዛ ምህረት ኣድርጎለት ይሆናል። መጀመርያ፡እንደ ነብዪ ያደረገው፡ ጌታ ምን እንደተናገረ ለማወቅ ሄደ። የጌታም ቃል ምን እንደሆነ ኣወቀ። እንዲህም አለ “ጌታን በዙፋኑ ተቀምጦ. . . የሰማይም ሰራዊት ሁሉ በቀኙ እና በግራው ቆመው ኣየሁ 'ስለሱ የተነገረውን ትንቢት እንዲፈጸም፣ ኣክዓብ እንዲወጣ የሚያሳስትልንማን ነው?' አለ።”

ኣያችሁ፡ ትንቢት፣ ኤልያስ ኣስቀድሞ “ውሾች ደምህ ይልሳሉ”ብሎ ተናግሮ ነበር።

ሚኪያስ ቀጥሎ “ሓሰትን መንፈስ ወጥቶ በፊቱ ቆመ፣ 'እኔወርጄ በአክዓብ ነብያት ኣንደበት ላይ ሆኜ ሃሰትን እንዲተነብዩ ኣደርጋቸዋለሁ' አለ።”

46 እንግዲህ እነዚህ ሰዎች በመለኮታዊ እውቀታቸው ብዛት የተነፉ መሆናቸውን እና የሚያስቡት ሁሉ እውነት እንደሚመስላቸው፡ ጌታ ያውቃል። ለዘመናቸው የተሰጠውን ቃል ፍጹም ኣላስተዋሉትም። ስለዚኣምላክም “ሂዱ ተከናወኑ” ኣላቸው። ሚኪያስ በክፉ መንፈስ እንደሚተነብዩ በተናገረ ጊዜ፡ የሚቃወማቸው በሰሙ ጊዜ፡ የቴለፎኑን መስመርይገነጥሉ ወይም ደግሞ ሬድዮውን ያጠፉ ወይም ኣንዳች ነገር ያደርጋሉ፣ ወጥተውም ይሄዳሉ። የሆነውን ግን ተመልከቱ። ሚኪያስ ያየውንራእይ ከቃሉ ጋር ማስተያየት ነበረበት፡ ከዛ በኋላ ያውቃል።

እንዲህ ብሎ አዘዛቸው "ተመልሼ ስመጣ . . . ወደ ግዞትጣሉት፣ የመከራ ውሃ እና የመከራም እንጀራ መግቡት፡ በሰላም ተመልሼ ስመጣ አሳየዋለሁ።" ኣላቸው።

ሚኪያስም "በህይወት ተመልሰህ ከመጣህ፡ ጌታ እኔን ኣልተናገረኝም።"አለው። ራእዩ ከዘመኑ ቃል አንድ መሆኑን የሚያውቅበት መንገድም ይህ ነው። የአክዓብ ጊዜ ነበር።

ወንድሞች እና እህቶች፡ ከባቢሎን የመውጣት ጥሪ አሁን ነው።የምሽት ብርሃኖች እዚህ ናቸው። ብርሃን ሳለ በብርሃን ተመላለሱ። ኣማኞች፡ የጌታ ቃል ሲገለጥ ያየሉ እንዲሁም እንደሚያምኑት ኣስተውሉ።ኢየሱስም "በጎቼ በዘመናቸው የሚገለጠውን ድምጼን፣ ቃሌን፣ ምልክቶቼን ያውቃሉ፡ ሃሰተኞቹ ግን ሊከተሉ ኣይቻላቸውም" አለ።

47 ከርእሴ ስወጣ እያየሁ ነኝና፡ እስኪ ወደ ጽሁፋችን እንመለስ።በጸሎቱ ሰልፍ ላይ በጣም ማተኮር እፈልጋለሁ። ለደቂቃ ያህል ከግምት ስር ስለገባን ኣሁን እስኪ ወደ ጽሁፋችንን እንመለስ። እንግዲህ ድሮም እንደነበረ ዳግም እንደ ድሮው ይደገማል።

ቃሉ በሚልኪያስ ምዕራፍ 3 "እነሆ መንገድን የሚያስተካክልመልእክተኛየን በፊቴ እልካለሁ" ብሎ የተሰፋቃል ተናግሮ እንደነበረ፡ኣምላክ ባርያውን ነብዪ ዮሃንስን ላከው። ዮሃንስም መጥቶ ስለሱ መሰከረ። እንዲሁም ነብዪ ኢሳያስ በኢሳያስ 40፡3 ላይ "የጌታን መንገድ ኣሰናዱ እያለ በምድረባዳ የሚጮህ ድምጽ እንደሚኖር"ሲናገር እናገኘዋለን። አያችሁ? እነዚህ ሁሉ ትንቢቶች! እንዲሁም - እንዲሁም ፈጽማችሁ አስተውሉት፡ ቅዱስ ቃላቶቹ የእርሱ መለያናቸው።

"አንተ ማነህ? መሲሑ ነህን?" ባሉት ጊዜ

"አይደለሁም።" አላቸው።

"ኤርሚያስ ነህን? ወይስ ከነብያት መካከል ኣንዱ ነህን?"

"አይደለሁም። ነብዪ ኢሳያስ እንደሚል፡ በምድረበዳ የሚጮህድምጽ ነኝ።" አላቸው።

የሚያምኑት ይመስልሃል እንዴ? በፍጹም አያደርጉትም። ለምን?በነሱ ቤተክርስትያን በኩል ስላልመጣላቸው አያምኑትም። የነሱ አልነበረም . . . አየህ፡ በዘጠኝ አመቱ ወደ ምድረበዳ ወጥቶ ሰላሳአመትሲሆን ተመልሶ መጣ። መልእክቶቹ መሲሑን የሚያስተዋውቅ ስለነበረ፡ ለስነመለኮት ትምህርት ቤቶች ከባድ መልእክት ነበረ። ሰውሁሉ እንዲህ ነው እንዲያ ነው ይለው ነበር። ጌታ ግን ከአባቱ ከዘካርያስ ሞት በኋላ ከምድረበዳ ላከው። እንዲሁም ካህን እንኳንቢኖር አባቱ የተከተለውን መስመር ግን አልሄደበትም።

ምክንያቱ፡ ነብያቶች በእምዲህ መልኩ አይላኩም። ከማይመችከምድረበዳ ምድር ይወጣሉ። ከየት እንደመጡ፡ ሜዳውስ ላይ እንዴት እንደተከሰቱ፡ ወይም ታሪካቸው የሚያውቅ ሰው የለም። ከሆነ ስፍራብቅ ብለው ቃሉን ይሰብካሉ፣ ኣምላክም ይወስዳቸዋል፡ በሄዱበትም ሁሉ፡ ታላቂቱን ቀን እየተጠባበቁ፡ ትውልዱን እየኮነኑ በቃሉ ጸንተው ይቀጥላሉ።

48 ስለዚ ከመካከላቸው አንዱ ስላልነበረ፡ ቤተክርስትያኒቱ አላመነችበትም።በሹመት መዝገባቸው ውስጥ ስለሱ መሾም የሚገልጽ መዝገብ ስላላገኙ፡ ተቃወሙት። አያችሁ፡ ቃል በቃል በግልጽ የተገለጠውን የጌታ ቃልለማመን ይቸገራሉ።አያችሁ? ሚልኪያስ 3፣ ስለሱ የሚመሰክሩ ሁለት ቅዱስ ቃላት ሚልኪያስ 3 እና ኢሳያስ 40፡3 በግልጽ አለ። አያችሁ እነዚህ ሁለት ቅዱስ ቃላት፡ መጥቶየጌታን መንገድ ስለሚያሰናዳ ሰው ያመላክታሉ። እሱም እያንዳንዷን ቅድመ ሁኔታ ያሟላ ሰው ነበረ።

ነብዪ ሊሆን ነበረ። "ኤልያስን እልክላቹኋለሁ።" እንዲሁም እነሆ በሚጎረብጥ በመንገድ ሁሉ ላይ ነበረ። ባህርያቱ ሁሉ ከኤልያስ ጋራ እንዴት እንደሚመሳሰል ተመልከቱት። ኤልያስ የበረሀ ሰው ነበረ፡ እንዲሁም ዮሃንስ፣ ከውጭ። ቀላል ሰው አልነበረም በጣም ከባድ ነበር።

እንደገና ይሄንን አስታውሱ፡ ኤልያስ ሴታሴትነትን የማይወድነበረ፡ ኤልዛቤልን ስለ መኳኳልዋ ሁሉ፡ ከየት ጀምራ እንዴት እንደምትወገድነገራት፡ ዮሃንስም እንደሱ። ኤልዛቤል በአማልክቶቿ ምላ፡ የኤልያስን ራስ እንደምትቆርጥ ዝታ ነበረች፡ ሄሮድያዳምእንዲሁ አደረገች። አያችሁ?

ስለዚ ሁልጊዜ መልእክቶቻቸውን አስተውሉት፣ የሚያደርጉትንእዩ። ወደ ኋላ ተመልሰው መጽሐፍ ቅዱሱ የሚናገረውን እና የሰውየውን ባህርያት ከቅዱስ ቃላት ጋር በመመዘን በዘመኑ ፍጹም ትክክለኛመሆኑን ቢመለከቱ ኖሮ፡ እሱ መሆኑን ማወቅ በቻሉ ነበር። ግማሽ ደርዘን ያህሉቱ አውቀው ነበር። አዎ በትክክል። በትክክል የተረዱትሰዎች ከግማሽ ደርዘን በላይ እንኳን አያህሉም። ሊሰሙት ወጡ ነገር ግን አላመኑበትም። አያችሁ? ለምን? በዘመናቸው የሚገለጠውንየትንቢት መለያ ምልክት ማወቅ ስለማይችሉ ናቸው።

49 "ትምህርት የለሌው መሃይም እብድ፣ የሚጮህ አውሬ፣ አደገኛ፣'ከባድ፣ ሸክም፣ ባዶ፣ የተቀዳ' እንዲሁም ሌላ ሌላ እያሉት" ይሰቁበት ነበር። ሁሌም እንደሚያደርጉት በትምህርቱ መጠን ፈረዱበት።በስዋስዋዊ ዕውቀቱ በአለባበሱ ፈረዱበት። በላዩ ላይ የበግ ቆዳ ለብሶበግመል መታጠቅያ የታጠቀ ሰውነቱ ሁሉ ጸጉራም ነበረ። ውሃ ባለበት ስፍራዎች፣ ወንበር የለው የስራባልደረባ የለው፣ አልተዋጠላቸውም፣የዚህን ዓለም አምላክ ያመልኩ ነበር። ኣያችሁ?

እንደነ እያኔስ እና እያምብረኔስስ ሐሰተኛ የሆኑ ነብያትአይነሱም እያልኩ አይደለም፡ ነገር ግን ልታደርጉት የሚገባችሁ፡ ኦሪጂናሉንመልእክት በቃሉ መርምሩት፡ ከዛ በኋልበየትኛው ዘመን እና ለዘመኑ የተነገረውን ትንቢት መለየት ትችላላችሁ።

50 የዮሃንስ ትንቢቶች ግን በራሱ በጌታ ትእዛዝ ማረጋገጫ ነበራቸው።እንዴት እውነት እንደሆነ ተመልከቱ። መጽሐፍ እንደሚል፡ "የጌታ ቃልወደነብዪው መጣ" ይላል። ቃል ማለት ደሞ ኢየሱስ ነው። ዮሃንስ ደግሞ ሊመጣ እና ሊገለጥ ስላለው ቃል ትንቢትን ተነበየ፡ ኢየሱስደግሞ ማለት ቃል፡ በውሆች ላይ ወደ ነብዪው መጣ። ኦ! እንዴት ድንቅ

ነው! የማይወድቅ . . . አያችሁ? በዘመኑ ላይ ከፍተኛየሆነ የቃል እጥረት ነበረ። በዚሁ ደግሞ “በምድረበደ የሚጮህ ድምጽ እኔ ነኝ” እያለ ነብዪ መጣ።

“ምን እናድርግ?” አሉ።

እሱም አለ “በመካከላችሁ፡ በአንድ ስፍራ ላይ አንድ አለ፡እኔ የእግሩን ጫማ መፍታት እንኳን ብቁ አይደለሁም፡ በመንፈስ ቅዱስ እና በእሳት የሚያጠምቃችሁ እሱ ነው። መንሹ በእጁ ነው፣ አውድማውምፈጽሞ ያጠራል። ስንዴውን ወደ ጎተራው ያከማቻል፡ ገለባውን ደግሞ በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል።” እንዴት ያለ ነብዪ ነው! ኢየሱስስለሱ ሲናገር “እስከዛ ዘመን ድረስ ከሴቶች ከተወለዱ መካከል እንደሱእንደሱ ያለ እንዳልነበረ” ተናገረለት። ከባድ ሩምሩምታ! ምን ላይ የቆመ እንደሆነስ እንዴት አወቀ? በትክክል ያውቃል። ከአምላክሰምቶአል፣ ከቃሉም ጋር አንድ ስለነበረ፡ ሰዎች ስለሚሉት ነገር አልተጨነቀበትም። እንዲሁ ሰበከው፡ እንዲሁም ትንቢትን ተናገረ።እንግዲህ አስተውሉ፡ አንድ ሰው ስለ እውነት ከቆመ፡ ጌታ ደግሞ የሰውየውንእውነት ለማረጋገጥ ግዴታ አለበት።

51 ሙሴ ወደ ግብጽ በወረደ ጊዜ “በዛ በምድረበዳ ማዶ ሳለሁ፡ እነሆ እሳትበላዩ ላይ የሚንቀለቀልበት ነገር ግን የማይቃጠል ቁጥቋጦ አይቼ ተጠጋሁ።ወደ ቁጥቋጦም በተጠጋሁ ጊዜ እነሆ ታላቁ የእሳት አምድ በላዩ ላይ ነበረ። ድምጽም 'እኔ እኔ ነኝ' አለኝ። እንዲሁም ይህችን ብትርይዤ ወደዚህ እንድመጣ እና፡ እነዚህ ተአምራቶችን እንዳደርግ ነገረኝ አለ። ስለዚ ጌታም ደግሞ ቃሉን ማረጋገጥ ነበረበት።” ብትሩምበዘረጋ ጊዜ፡ እነሆ ዝንብ እና ቁንጫ እንዲሁም ጭጋግ፡ ጨለማ እና ሌሎች ሆነ። ከዛ በኋላ የነብዩን እውነትነትለማረጋገጥ፡ እነዚያን አማኞች ወደ ተራራው ስር አመጣቸው፡ በዛውበተራራው ራስ በዛ በእሳቱ አምድ ወርዶ ተገለጠ፡ እውነተኛ መኖሩንም አረጋገጠላቸው።

እንግዲህ በኛ በዚህ ዘመን ደግሞ ያደረገውን ተመልከቱ።

52 ቃሉ፡ ወደ ነብዩው ይመጣል፣ ቅዱስ ቃላት ይመጣል ወደሚሉትሰው ይመጣል፡ የሰውየውም እውነትነት ያሳያል። እንፍጠን አሁን። ኢየሱስ ሲመጣ ሰው - ሰራሽ ከሆነ የትንቢት ትርጉም በተለየ መልኩመጣ። ሰው ሁሉ የየራሱ ትርጉም አለው። ፕርስቢተርያኖች ከነሱ መካከል እንደሚሆን አድርገው ያስባሉ። ጌታ አንድን ነገር ሲያደርግአስተውሉ፣ ሌሎች ድርጅቶችም እንዲሁ ሲነሱበት ተመልከቱ። አዎ ከድሮም እንደዛው ነበረ። እያኔስ እና እያምብሬነስ ሁለም አሉ። እነሱሁሌ ቃሉን ቆርጠው ይናገራሉ። በነብዩው መሰረት ግን፡ እያንዳንዱን ቃል ጭምር!

53 አሁንም እንደወትሮአቸው አላወቁትም፡ ኮኮብ - ቆጣሪ “ዲያብሎስ፣ቢኤል ዘቡብ” አሉት። እንዲሁም በራሳቸው መጽሐፍ ተረድተው አምላክመሆኑን መረዳት እየቻሉ፡ ደግሞም አምላክ ነኝ ይላል ብለው ከሰሱት።

በኢሳያስ ምዕራፍ 9፡6 ላይ ስለሱ “ስሙም ሃያል አምላክ፣ የዘለአለም አባት”እንደተባለ አስታውሱ። ከመጀመርያም ጀምሮ የነበረ አባት እሱ ስለሆነብቻውን እሱ አባት ነው። ከዛም በኋላ ሌሎች አባቶቻችን የሚሉአቸው አይኖራቸውም። “በዚ ምድር ላይ ከሚገኙ ሰዎች መከካል አባትብላችሁ አትጣሩ” “ሃያል አምላክ እና ዘለአለማዊ አባት እርሱ ነው፣ ድንቅ መካር፣ የሰላም አለቃ።” በርግጥም።

እንግዲህ አሁንም በዚህ በሎዶቅያ ዘመን ከቤተ ክርስትያንውጪ ለማድረግ እያደረጉት እንዳሉት ሁሉ ነብያቶች ሁሉ የተደረገባቸውን ሁሉ ያደርጉበታል። “እውርነታቸውን እና ራቁትነታቸውን አያውቁትም።”ነብያት እንዳሉት፡ የመጽሓፍ ቅዱስ ነብያት። ስለነሱ በትንቢት እንደተነገረ፡በሰው ባህል ታውረው፣ እንደድሮአቸው አሁንም ቃሉን ከቤተክርስትያናቸው ያወጡታል።

54 አሁን አስተውሉ፡ ሳትረዱት እንዳያልፋችሁ፡ ፈጠን ፈጠን በሉ። ኢየሱስ ለሁለቱም ደቀመዛሙርቱ፡ እሱ መሲሐቸው እንደሆነ ያስረዳበት ጽሁፍ እነሆ! አይኖች ሁሉ ወደዚህ ያትኩሩ።በምድሪቱ ያላቹ ሁሉ ይሄንን እንዳያልፋችሁ። መጽሓፍ ቅዱስ፡ ከአምላክ ከራሱ፡ በሰው ከንፈር እና በሰው አገልጋይነት የተጻፈ የጌታቃል መሆኑን ልንነግራችሁ ሞክረናል። አምላክ ራሱ መጻፍ ይችላል። አምላክ ራሱ መናገር ይችላል። አምላክ ማድረግ የወደደውን ነገርሁሉ ማድረግን ይችላል። ነገር ግን ሰው የአምላክ ክፍል ስለሆነ፡ ማድረግ የወደደውን ሁሉ እንዲያደርግለት ሰውን ይመርጣል። ስለዚአምላክ ነው መጽሓፍ ቅዱስን የጻፈው። እንዲሁም ሰዎቹ፡ በስጋዊ አስተሳሰባቸው ስለሚጽፉት ነገር እውቀት አልነበራቸውም። ምናልባትምላይስማሙበት እኮ ይችላሉ፡ ይሁን እንጂ ጻፉት። አይችሉም። መጽሓፍ ሲናገር፡ “ሰዎች፡ በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው!” ይላል። አምላክእጆቻቸውን አንቀሳቀሰ፡ እንዲሁም ዐይኖቻቸውን በራእይ ነዳ። ከሚያዩት ነገር ውጪ ምንም ሊሉም አይችሉም። 'አንደበታቸውን ሁሉ ጣቶቻቸውንእና የአካሎቻቸው ክፍል ሁሉ በኣምላክ ሙሉ ቁጥጥር ስር' ስለሆነ ሌላ መናገር አይቻላቸውም። መጽሓፉ አማልክት ቢላቸው አይገርምም፡የአምላክ ብልቶች ስለነበሩ። እሱ የአምላክ ሙላት ነው።

55 አሁን አስተውሉ፡ ኢየሱስ! ማለቴ ቃል እነዚያን ልቦቻቸውን ተሰብሮባቸው የነበረውን ሁለቱን ደቀመዝሙርን፡ መሲሐቸው፣ መሲሑ፣ የተስፋው ቃል እሱ እንደሆነ እንዲያውቁት አደረጋቸው። ያደረገውን አስተውሉት፡ትንቢትን ነው የጠቀሰላቸው። “እናንተ ሞኞች፡ በነብያት የተጻፈውን ለማመን የዘገያችሁ” አላቸው። እንግዲህ “ቤተክርስትያኒቱ ስለዚጉዳይ ምን ምን አለች?” አላለም።

ምን ምን እንደተከናወነ ያውቁ ስለነበር፡ የተፈጸመውን ሁሉታሪኩን አጫወቱት። አዝነው ነበር። “አንተ ብቻህን እንግዳ ነህን! ወይስ በኢየሩሳሌም የተደረገውን ነገር አታውቅምን?” ይሉት ጀመር።

ልክ እንደ የማያውቅ በመምሰል “ምን ነገር?” በማለት ጠየቃቸው።አያችሁ፡ አንዳንዴ በነገሮች ላይ እንዴት እንደምታደርጉ

“አንተ እንግዳ ነህን?” የሚያናግራቸው ሰዎች እኮ፡ ለሶስትአመት ተኩል አብረዉት የኖሩት ሰዎች ናቸው። ነገር ግን አላወቁትም።

“ምንድነው ነገሩ?” “ምንድነው የሆነው?”

መልካም፡ እንግዲህ “ነብዩ መሆኑ በፍጹም የማንጠራጠርበት፡የናዝሬቱን ኢየሱስ። በህዝቡ ፊት ሁሉ፡ በቃልም በስራም የበረታ ነበረ። በዚ ዘመን የጌታን ነብዩ መለያ የሚሆኑትን ምልክቶችን ኣይተንበታል።ይሄንን እናውቃለን። ኢስራኤልን የሚበዥ አዳኝ ነው ብለን ተስፋ አድርገንበት ነበርን።”

እሱም ዞር ብሎ “እናንተ ሞኞች፡ ልባቹ ነብያት ስለሱ እንዲፈጸምየጻፉትን ለማመን የዘገየ፡ ነብያት ስለሱ የጻፉት እንዲፈጸም አይገባምን?” አያችሁ? ወደ ትንቢቱ ለመመለስ፡ አሁን ብኣትኩሮት ተመልከቱ። እናምነዋለን ለሚሉ አማኞችነን ባዮች እንዴትያለ ግሳጼ ነው!

56 ጉዳዩን እንዴት እንደፈታላቸው አስተውሉት። እሱ እንደዛነውና ማለትን እየቻለ፡ እንዲሁ መጥቶ “መሲሐቹ ነኝ” አላላቸውም። ነገር ግን አሁንም አስተውሉት፡ እነሱ እንዲያውቁት ራሱን ከቃሉ ጋር አስተያየላቸው። ማለት ቢፈልግኖሮ ማለት ይችል ነበር፡ ይሁን እንጂ እነሱ የአምላክ ልጆች ከሆኑ፡ ነብያት ሁሉ ስለሱ በተናገሩት ነገር ላይ ተነስቶ መናገር በጀመረጊዜ፡ በራሳቸው መመስከር ይችላሉ። ነገር ግን አትኩሮታቸውን ሁሉ ነብያት ወዳሉት ስቦ፡ መሲሑ በሚገለጥበት ዘመን የሚሆነውን ነገርእንዲመለከቱ አደረጋቸው። ዮሃንስ፡ መልእክታቸውን ከመጽሓፍ ቅዱስ ማለት ከቃሉ እንዲለዩ አደረጋቸው። የትኛውም እውነተኛ ነብዩም የሚያደርገው እንዲህ ነው። እንዲሁወጥቶ “እኔ እሱ ነኝ፣ እኔ . . . አላለም።” እውነተኛ የአምላክ ነብዩ እንዲህ አደለም። አያችሁ? ነገር ግን እሱ እንዲህ አላቸው“ተመለሱ፡ ቃሉት ተመልከቱት” አላቸው። አያችሁ፡ አሰራሩን ፈጽሞ አያሳስትም። አያችሁ?

“ሙሴን እናውቀዋለን” ስላሉት፡ እንዲህ አላቸው።

“ሙሴን ብታውቁት ኖሮስ እኔን ደግሞ ባወቃችሁኝ ነበር” አላቸው። “ሙሴ ስለእኔ ጽፎአልና” አላቸው። እንዲህምደግሞ አላቸው “በእነሱ የዘላለም ህይወት የምታገኙ ስለመሰላችሁ፡ ቃላትን ትመረምራላችሁ፡ እነሱም ስለእኔ የሚመሰክሩ ናቸው። ሂዱእና ቃላቶቹን አስተውላችሁ እዩዋቸው።”

57 እነሆ እሱ አሰራሩን ፈጽሞ አልለወጠም፡ አሰራሩን ለውጦምአያውቅም። እሱ የማይለወጥ አምላክ ስለሆነ ፈጽሞም አሰራሩን አይለውጥም። አያችሁ? እናም እሱ ወደ ኤማሁስ ይጓዙ ወደነበሩት ሁለቱምደቀመዝሙርት ቀልዮጳ እና ጓደኛው ጋር ቀርቦ “መሲሁ ሲመጣ ስለሚፈጽማቸው፡ ነብያት ሁሉ የጻፉትን ባለማመናችሁ የምትሞኙት ስለምንድነው?”በማለት ቅዱስ ቃሉን አቀረበላቸው። ኦ! እንዴት ያለች ድንቅ ቀን!

ዮሃንስም እንዲሁ አደረገ፡ “ቅዱሱን ቃል መርምሩ፡ 'በምድረበዳየሚጮህ ድምጽ' ይኖራልና።” እኔስ ከየት መጣሁ? አያችሁ? ይሄንን ነው ለነሱም ግልጽ ሊሆንላቸው የሚገባው። አዎ!

መንፈስ ቅዱስ ሲሰራቸው የምንመለከታቸውን ነገሮች፡ ዛሬግልጽ መደረግ አለባቸው። አንዴ “ቅዱስ ቃላትን መርምሩ” ብሎናል። እኛም ደግሞ . . . ዛሬ እንድናደርገው ይፈልገናል።

58 በሙሴ ትንቢት እንደጀመረ አስታውሱ፡ መጽሓፍ እንደሚል፡ “ከሙሴ ጀምሮ፡ ሙሴ እና ነብያት ሁሉ” ነገርግን በሙሴ ነው የጀመረው።“ያ ነብዩ” አለ ሙሴ። “እናንተ ሰዎች ሆይ ጌታ አምላካችሁ ከመካከላችሁ ነብዩን ያስነሳል።” አላቸው።

እንዲህ ማለት እኮ ይችል ነበር “አንተ ኪልዮጳስ እና ጓደኛው፡ሙሴ በነዛ ቀናት ጌታ ኧምላካችሁ ነብዩን ያስነሳል አላለምን? እናምይሄንን ሰቀሉት የምትሉትን ሰው፡ እነኚህን ቅድመ ሁኔታዎችን ኣያሟላምን? እንግዲህ ሙሴ እንዲህ ከተነበየ፡ እንዲሁም ደግሞ ለብዙመቶ አመታት ነብዩ አልነበራችሁም፡ እነሆም ይህ ሰው ማጣ። የዚህንሰውየ መንገድ ጠራጊስ ምንድን ነበር ያለው?” ገባችሁ? እንዲሁም ሌሎች ነብያቶች ስለሱ ዘመን የተናገሩትን ሁሉ ነገራቸው። በርግጥምእሱ ሲናገር መስማቱ ደስ ያሰኛል። እሱ ሲናገር መስማት አትወዱምን? እኔ እሱ ነኝ እኮ አላለም ነገር ግን ነብያት ሁሉ ስለ ገዛራሱ የተናገሩትን ሲያወራ መስማት እኔ እፈልጋለሁ። በቃ እንዲሁ ከትንቢት አሳያቸው። “ነብያቱ እንዲህ ይሆናል ብለው ያሉትን” አሳያቸው።አያችሁ?

59 ትንሽ ደቂቆችን ወደ ኋላ ተመልሰን፡ በሱ የተነገሩትን ቃላትንእስኪ እንስማቸው። እዚጋ ቃሉ ራሱ ስለ ራሱ እየጠቀሰ እንዳለ አስተውሉ። ቃሉ ራሱ፡ ስለ ቃሉ ይጠቅሳል። እሱ እንደዛ መሆኑን በመናገር አይደለም። ነገር ግን ቃሉ ራሱ ስለራሱ ይናገር፡ ከዛ በኋላእሱ ማን እንደሆነ ያውቃሉ። የቃሉ ፊደላት ቃሉን ይጠቅሳሉ . . . በስጋ ያለው ቃል ሙሉ ለሙሉ ከራሱ ጋር እያስተያየ የፊደሉንቃል ይጠቅሳል። እንግዲህ እስኪ የጠቀሳቸውን ነገሮች እስኪ እንመልከታቸው። እንዲሁም ደግሞ አሁን አስቀድመንም እንዳነበብነው፡ ስቅለቱን፣ መቃብሩን፣ እና ትንሳኤውንበተመለከተ እንዴት ግልጽ እንደተደረገላቸው ማወቅ እንችላለን። በቀጥታ ስለሱ ወደ ተነገሩት የትንቢት ቃላት ሄደ። እስኪ ለምሳሌ እንዲህ ብሎአቸዋል ብለን እናስብ፡ ከዚህም በላይ ብሏል ይሁን እንጂ፡ ተመልከቱ።

60 እንዲህ ሲል . . . ሲል ይሰማ እንበል፡ “እስኪ ወደ ዘካርያስ 11፡12 እንክፈት፡ እንደ ነብዩውስ ትንቢት በሰላሳ ብር ሊሸጥየተገባው መሲሑ አልነበረምን? እናንተም እንደምትሉት፡ ይህ ሰው በሰላሳ ብር እንደተሸጠ ብላቹኋል።” እስኪ አስቡት፡ ቃላቶቹን አገኛቹኋቸው?ዘካርያስ 11፡12። እንዲህም አላቸው “ዳዊትስ በመዝሙር ያለውን አስተውላቹኋልን? መዝሙረ ዳዊት 49፡9? ወዳጆቹ ይከዱት ዘንድእንዳላቸው። እንዲሁም ደግሞ በዘካርያስ 13፡7 ደቀመዝሙርቱ ጥለውት እደሚሄዱ። እንዲሁም በመዝሙረ ዳዊት 35፡11 በሐሰት ምስክሮች እንደሚከሰስ። እናንተም ብላቹኋል። ኢሳያስ53፡7 በከሳሾቹ ፊት ዝም ይላል። ኢሳያስ 50፡6 ላይ፡ ነብዩው እንደሚገረፉት ተናግሮአል። መዝሙረ ዳዊት 22 በመስቀል ላይ ሆኖ'አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ?' ይላል። ከትላንት ወድያ ከሰዐትስ እንደዛ ብሏልን? እንደገና መዝሙረ ዳዊት22 እንዲሁም 18 ልብሱን ዕጣ ይጣጣሉበት እንዳላቸውይገልጻል። እንደዛስ አደረጉበት? መዝሙረ ዳዊትስ 22፡7 እስከ 8 ጠላቶቹ ማለት ቸርቿ እንደሚያላግጡበት። መዝሙረ ዳዊት 22 ከአጥንቶቹየሚሰበር እንደለለ 'ነገር ግን እጆቹን እና እግሮቹን እንደሚበሱ' ተናገረ። ያለጥርጥር በዛ ሰዐት ላይ ሁለት እጆቹን ወደ ኋላአጣምሮ። ከኢሳያስ 53፡12 ጠቅሶ በሁለት ወንበዴዎች መካከል ሆኖ እንደሚሞት፡ ተናገራቸው። ኢሳያስ 53፡9 ከሃብታሙ መቃብር እንደሚቀበር።መዝሙር 16፡10 'ነፍሱን በሲኦል እንደማይተው፡ ቅዱሱም መበስበስን እንደማያይ።' የዚህስ

ሰው መንገድ ጠራጊ በሚልኪያስ ምዕራፍ3 ያለውን አይደለምን?” አ! እነኚህን ጥቅሶች ሲናገር መስማትን እመኛለሁ። ትንቢቶቹን ተመልከቱአቸው! እሱ ያለፈበትን ጥላዎችሁሉ አስተውሉአቸው። ይስሀቅ በዘፍጥረት 22 ላይ ጌታ ይስሐቅን በጥላ እንዴት እንደተጠቀመበት፣ አባቱ አብርሀም እንጨትን አሸክሞእንዴት ወደ ተራራው እንዳወጣው፡ በዛዝ አንድ ልጁን እንዴት እንዳቀረበ ተመልከቱ።

61 አሁን ወደ ውስጣቸው መዝለቅ ጀመረ። ስለ ቀናቸው የተነገረውን ትንቢት ባለመመልከታቸው ምክንያት ሞኞች ብሏቸዋልና። አሁን ግን ሊገባቸው ጀመር፡ ከጥቂት ቀናት በፊት ባለፉት ሁለት ሶስት ዓመታት የተፈጸመውን የዘመኑ እርግጠኛ ትንቢት እንዴት እንዲፈጸም ማስተዋልጀመሩ። ያኔ ነበረ የተሰቀለውን ወዳጃቸውን ኢየሱስ፡ እነዚህን ቃላቶች ሁሉ መፈጸሙን ያስተዋሉት። አ! የዛኔ ነበር ሰውየው መሲሑመሆኑን የተረዱት - ከሙታንም እንደሚነሳ የተረዱት። “መቃብር ሊይዘው አይችልም 'ቅዱሱንም መበስበስን ያይ ዘን አይተወውም' ከትንቢትቃልመካከል የምትወድቅ የለችም። እሱ ተነስቷል።”

62 “እንግዲያስ እነዛ፡ ዛሬ ማለዳ ከመቃብሩ መልእክት ይዘው የመጡትም እውነት ናቸው። እሱ ከሞት ተነስቷል፣ ህያው ነው፣ እሱ መሲሕ ነው።” ለምን? [ወንድም ብራንሀም ሶስት ጊዜ አጨበጨበ] ሳይገባችሁ እንዳያልፋችሁ። “ድርጊቶቹ፣ አገልግሎታቱ እና ያደረጋቸውን ነገሮች ሁሉ ነብያት በዚ ቀን ይሆናል ባሉት መሰረት የተረጋገጠነበረ። ይሄው ነው።” ያኔም ይሄንን ሁሉ ያደረገ እሱ ወዳጃቸው ኢየሱስ እንደሆነ አወቁ። ሲናገራቸው በልባቸው ውስጥ ቢነድባቸውምአይገርምም። አጭር ጊዜ እስኪመስላቸው ድረስ ስድስት ማይልስ ያህል ተጓዙ።

63 ሌላ ያደረጉት ነገርም ይህ ነው፡ ለስድስት ሰዐታት ሙሉየትንቢትን ፍጻሜ ስብከት እየሰሙ እንደነበረ ታውቃላችሁ። በመንገድ ሁለ የነገራቸውም ይህ ነው። ልክ መንገዳቸውን በጀመሩ ሰዐት፡እሱም በኢየሩሳሌም ነበረና እሱም መንገዱን ጀመረ። ከስድስት ሰዐታት በኋ . . . በኋላ ስድሳ ምዕራፍ በኋላ ኤማሁስ ለመድረስስድስት ማይልስ ርቀት በመንገድ ላይ ነበሩ። እንደዛ ነው። እንዲሁም ደግሞ የስድስት ሰዐታት ትንቢትን ማረጋገጥን በተመለከተ ስብከትሰበካቸው። በኔ ሶስት አትኮኑኙኝ እና ተመልከቱ። አያችሁ? መሰበካቸውንግን አስተውሉ . . . እሱ . . . የተገለጠውን ትንቢት በማረጋገጥ ዙርያ የስድስት ሰዐታት ስብከትን ሰምተዋል።

64 እንግዲህ እየመሸ ነው። እሱ ትላንትናም ዛሬም እስከዘለአለም ድረስ ያው እንደሆነ ታውቃላችሁ። በዛን ሰዐት ነበረ፡ ትላንትናም ዛሬም እስከ ዘለኣለም ድረስ ያው እንደሆነ ዕብራውያን13፡8 እንዲያስተውሉ ዐይኖቻቸውን የከፈተላቸው። ሲመሽ ነገሮች ሁሉ በትንቢት ይበራሉ። በጊዜው የሚገለጸውን ትንቢትን ካመናችሁ፡በሰለጠነው ዘመን እየሆነ ያለውን ነገር በቀላሉ መለየት ትችላላችሁ።

“አዎ እናንተ ሞኞች፡ ለማስተዋል የዘገያችሁ፣ ነብያት ሁሉመሲሑ ስለሚደርስበት የተናገሩትን ለማመን የምትዘገዩ (በአንድ ጉዳይ ብቻ መዞር) ሊፈጸምበት አይገባምን?” እንግዲህ መጀመርያ እነዚህንየመሳሰሉትን ነጥቦችን ፈትሾ፡ ነብያት ስለሱ .ያሉትን ሁሉ አሳያቸው። ከዛ እነሱም ይገባቸው ጀመረ። ከዛም እንዲህ አላቸው .. . መንገዱን እንደሚቀጥል አስመሰለ። ይሄንን ሰው በጣም ወደዉት ነበር “ዛሬ አስበናው የማናውቅ ነገር ሰጥተሀናል፡ እንግዲህበሆነ ስፍራ ህያው ሆኖ አለ” አሉት። እሱን ያናግሩታል ነገር ግንአላወቁትም። እናም እሱ . . . ያለ ጥርጥር በሃዘኔታ ተመልክቷቸው መንገዱን መቀጠል ጀመረ፡ ይሁን እንጂ ወደ - ቤታቸን እንዲጋብዙትይጠባበቃቸው ነበር። ዛሬም የሚፈልገው ይህ ነው፡ እንድትጋብዙት ይጠብቃቹኋል።

65 እንግዲህ አስተውሉ እነዚህ ደቀመዛሙርት በገበታ ዙርያ ሕብረትእንዲያደርግ በጋበዙት ጊዜ፡ ከመሰቀሉ በፊት አድርጎት እንደነበረ አንዳች ነገር ያደረገው ያኔ ነበረ፡ ዐይኖቻቸውም ተከፈቱ። አሰራሩንአደራረጉን ያውቃሉ። ከዚህ በፊት ያደረገዉ እና አሁን የሚያደርገውን ካሁን በኋላም የሚያደርገውን ያውቃሉ። “ጌታ እርሱ ነው!”ብለው ለመጮህ በተነሱበት ጊዜ ከአጠገባቸው ተሰወረባቸው። እንግዲህእነዚህ ይሄንንን ስብከት ለመስማት ስድስት ሰዐታት የፈጀባቸው ሰዎች “እርሱ ህያው ሆኖአል ተነስተዋል” ብለው ለመናገር እግሮቻቸውን- ለማፍጠን ምናልባት ሃያ ደቂቃም አልፈጀባቸውም ይሆናል።

66 ወዳጆች ሆይ ይህ ሁሉ የሚልኪያስ 4፣ ሉቃስ 17፣ ዮሃንስ15 እንዲሁም ይሄንን ዘመንን አመላካች የሆኑትን እንደ ራእይ 10 እና ሌሎችን ብዙ ቅዱስ ቃላት ፍጻሜ ነው። በተጨማሪም በማርቆስእና በማቴዎስ መጽሓፍቶች በሰማይ ስለሚታዩ ድንቅ ምልክቶች በተናገረበት መሰረት፡ በሓሳብ ቅጽበት - በፍጥነት ከእይታ የመሰወርብቃት ያላቸው፡ ሰዎች የማይታወቁ መንኮራኩሮችን፣ በራሪ መንኮራኩሮች ብለው ስለሚጠሯቸው ያወሳል። ጌታ መጻፍ፣ መናገር ይችላል፣ማድረግ የወደደውን የማድረግ ችሎታ አለው። “ትላንትናም ዛሬም እስከ ለዘለኣለም ያው የሆነው” ድንቁ የእሳቱ ዐምድ። ከምድር ሰላሳማይልስ ወደ ላይ ርቆ እርጥበት በሌለበት እንዲሁም ምንም በማይገኝበት ከፍታ ላይ፡ ከመሬት ወደ አየር ላይ የሚነሳ የፒራሚድ ደመናሲወጣ ታይቶአል። ይሄም ደግሞ እንደሚሆን፡ ከአንድ አመት ተኩል በፊት ይሆናል ተብሎ ግምታዊ ትንቢት ተደርጎለት ነበር። እስኪ ያንንስእልን ገልብጣችሁ እዩት እና፡ ማንንን እንደሚመስል ተመልከቱ። ከተባለው ቃል አንድም ወድቆ አያውቅም፡ እዚህም ደግሞ የእውነታውን ማረጋገጫ ይሆን ዘንድ፡ ይሄው የጌታቃል እዚህ አለ። አሁን እንደገና አመሻሹ ላይ ደርሰናል። ዛሬስ በጸጋው ይመለስ ይሆን ወይ፤ ድሮስ እንዳደረገ አንዳች ነገር ያደርግይሆ ን ወይ ብየ አስባለሁ። እስኪ እንጠይቀው፣ እንጸልይ፤ በተረጋገጠ ትንቢት የተገለጹ ኩነቶች።

67 ሁሉን ቻይ አምላክ ሆይ እርዳን፤ እንድናስተውለው እና እንድንረዳው የሚገባንን እንድናውቅ እንድትረዳን፡ ቃልንህን እንድናስተውል፡ የተወደድክ አምላክ ሆይ እርዳን። አሁንም ጌታ ሆይ ላለፉት ሁለትሺህ ዐመታት የመጻሕፍት ጽሑፎችን ስብከት ሰምተናል። በዚህም በመጨረሻ ቀናት እንደገና ተነጥፎአል፣ ወደ ማምሻም ጊዜ ሆኖኣል። ሜተዲስታውያን፣ባብቲስታውያን፣ ፕሪስቢተርያኖች እንዲሁም አብዛኞቹ፡ በዘመናት ሁሉ ከአንተ ጋር ተነጋግረዋል፡ ምናልባትም ቀንም ማታም ባልሆነበትበታላቁ ቀን መንገድ፡ ነብዪው እንዳለ፡ ሲመሽ ብርሃን ይሆናል። ኢየሱስ ከመቃብር ተነስቶ ለስምዖን እና ለሴትዋ ታየ፡ ህያው መሆኑንምአሳያቸው። ያ ጥዋት ነበረ። እንደገናም በማታ ጊዜ

ተመልሶ መጣ። ስለ መታወራቸው እንዲገስጻቸው፡ በቀን ከእነርሱ ጋር ተራመደ፤ በመሸም ጊዜ ራሱን ገለጠላቸው።

68 አምላክ ሆይ፡ በዚህ ምሽት በቃልህ ዙርያ ባደረግነው ህብረትና። አምላክ ሆይ በዚህ ጊዜ የሚያምን ብዙ ሰው የለም ይሁን እንጂ "አባቴ የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣሉ" ብለህ በቃልህ እንደተናገርክ፡ለዘላአለማዊ ህይወት የወሰንካቸው ስላሉ፡ ምስጋናየ ብዙ ነው። አሁን ደግሞ፡ የምሽቱ ብርሃን በሚያበራበት ወቅት፡ አንተ ከፈቀድካቸው (ከተፈጸሙት በመቶዎች የሚቆጠሩ) ከትንቢት አንድን እንኳ እንዳይወድቅ እንደፈቀድክ አንድ እንኳን አልወደቀም። ይሄንን የሚያመላክተውካለውስ፡ እንግዲያስ አንተን ነው፡ ምክንያቱ ሰው ሆኖ እንዲህ አይነት ትክክል ሊሆን ስለማይችል። ልክ እንደ መጽሓፍ ቅዱስ፡ በአስራስድስት መቶ አመታት፣ በአርባ የተለያዩ ሰዎች ተጽፎ ያለ አንዳች ስህተት ሊጽፍ፡ ማንም አይችልም። የተወደድክ አምላክ ሆይ፡ ዛሬ ራስህን እንደ ዕብራውያን13፡8 ትላንትናም ዛሬም እስከ ዘለአለም ያው መሆንህን እንድትገልጽልን እጸልያለሁ። "በዚ በመጨረሻ ዘመን ላይ ዐለም እንደ ሰዶምእና እንደ ጎመራ በተበላሸችበት ዘመን" ተስፋ ሰጥተሀል። ትላንትናምያደረግከው ዛሬም አድርግ። እንደ ሴት የለበሱ፡ ሴት የሚመስሉት ወንዶችን ይታያሉ እንዲሁም - እንዲሁም ወንድ ለመምሰል የሚጥሩሴቶች እየተመለከትን እንገኛለን። በተበላሸው ትውልድ ውስጥ የሚኖሩ ሴቶችም ወንዶችም አየን። የጾታ መስህብ ጣኦት አምልኮ የሆነበትጊዜ ደርሷል። ወንጌል ወደ አንድ ጥግ ተገፍቷል፡ በሎዶቅያ ቤተክርስትያን ዕርቃን በዝቷል። ኦ አምላክ ሆይ፡ ምን ዓይነት ጊዜ ደረስን! ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና 'ና ራስህን ግለጥልን። በኢየሱስ ስም ለምነናል እና።

69 እንግዲህ ራሶቻችሁ ዝቅ ብለው ዐይኖቻችሁ ጨፍናችሁ ሳላችሁ፡አንዳች ነገር እጠይቃችኋለሁ። አምላክ እዚህ እንዳለ ታምናላችሁ? ዛሬ በዚህ ቀን እየተከናወነ የሚገኝስ ነገር የትንቢት ፍጻሜ እንደሆነታምናላችሁ? ኢየሱስ ክርስቶስስ ትላንትናና ዛሬ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው እንደሆነ ታምናላችሁን? እሱ በስጋ ወራቱ በስጋ በነበረበትወቅት ያደረጋቸውን ነገሮች አሁንም በዚ ዘመን እንደሚደገሙ ታውቃላችሁን? ነብዪውም እንደዛ ብሏል፣ መጽሐፍ ቅዱስም እንደዛ ብሏል።ቃል ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ግድ ነው፡ ፈጽሞ አይወድቅም። ራሱን እንዴት ነበር ያስታወቀው? ሙሴ የተናገረለትን ያንን ነብዪ በመሆን፣የህዝብ ልብን ሚስጢር በማወቅ። ያቺ ሴት የልብሱን ጫፍ ስትነካ፡ ወደሷ ዞሮ "እምነትሽ አድኖሻል" አላት። ስምዖን ወደ'ሱ በመጣጊዜ፡ ስሙ ማን እንደ ሆነ እርሱ ራሱ ማን እንደሆነ፣ የአባቱንም ስም ጭምር ነገረው። አሁንም ቢሆን ይሄን ውድ ኢየሱስ አልሞተም፡ለዘለአለም ህያው ነው። ክብር ለጌታ ይሁን! አሁንም በዚህ የማምሻ ዘመን ላይ፡ ዳግም ሁላችንም በህብረት እየጠራን መሆኑን አምናለሁ።

70 ኦ ጌታ ኢየሱስ፡ ሆይ ናልን በመሀላችን ሁን። አትለፈን።ይሄን ለሊት እስኪያልፍ ድረስ፡ ጌታ ሆይ ለሊቱን ሙሉ አብረሀን ሁን። በትንሳኤህ ጉልበት እናውቅህ ዘንድ፣ እንዲሁም ፍቅርህ፣ ጸጋህእና ምሕረትህ ከእኛ ጋር ይሆን ዘንድ፡ ነገ አብረንህ እንሂድ። ኦ ዘለአለማዊ አምላክ ሆይ፡ እነኚህን ነገሮች ማድረግ የሚችለውንአምላክ ብቻውን ነውና አንተ አድርግልን።

በዚህ ጸጥ ባለው በተረጋጋ ሰዓት ላይ እንዲህ እንበል፦ አባታችን የሆንክአምላካችን፡ ስጋችን ደካማ ማደርያህ ነው። ነገር ግን ጌታ ሆይ፡ የሚቀድሰንን ጸጋህ፣ መንፈስ ቅዱስህ አሁን ይምጣልን። እንደ ጴጥሮስሳንጠራጠር ተነስተን "አንተ ክርስቶስ፡ ትላንትናና ዛሬ እስከ ዘለአለም ያው ነህ።" ብለን በድፍረት እንድንናገር በኛ ውስጥ ካለውጥርጣሬዎች እና ግራመጋባት፣ ካለመጽናት እና ከጥርጥር መንገድ አንጻን።

71 ጌታ ሆይ ቃልህ እውነት እንደሆነ እናምናለን። ለሰልፉ ጸሎትከመጀመራችን በፊት ጌታ ሆይ፡ ራስህን ስትገልጥልን እናይ ዘንድ አድርግ። "በሎጥ ዘመን እንደነበር" ብለህ እንደተናገርክ፡ እነዛየተጠሩቱ - እነ አብርሀም የተስፋውን ልጅ ሲጠባበቁ ሳሉ፤ ሎጥ እንደ ህዝብ ለየሀይማኖት ተቋም የተነገረውን ዘመናዊው የቢሊ ግራሀምእና የኦራል ሮበርትስ ድምጽ ይሰማ ነበር። አብረሀም ግን ያለ ተቋም ነበር። እነዚያ ትንሽ መንጋ ሊወርሷት ባለች ምድር ላይ ታችይሉ ነበር። "ትሁታን ምድርን ይወርሳሉ ነውና።" አንድ ቀን በዛፍ ጥላ ስር ተቀምጠው አርፈው ሳሉ፡ አምላክ በሰው አምሳል መጣላቸው።ሁለቱ መላእክቶች ወደ ሶዶም ወረዱ። በሰው ስጋ የተገለጠው አምላክ ግን አብርሀምን "አብርሀም፡ ሚስትህ ሳራህ የት ናት?" አለው።ከጥቂት ቀናት በፊት አብራም ይባል ነበር፡ እንዲሁም ሚስቱ ሳራይ፡ ሳ-ራ-ይ ትባል ነበር፤ ሳራህ "ልዕልት" አልነበረችም። በልዕልትስሟ በንጉስ ልጅ መጠርያ ጠራሀት። አብርሀምን በስሙ ጠራሀው፡ አብርሀም የትውልድ የህዝብ አባት አልከው። እንዲሁም "እጎበኝሃለሁ" ብለህ አልከው።

72 አምላክ ሆይ፡ የዛን ነብዪ ልብ እንዴት ዘሎ ይሆን! ያኔማን እንደነበርክ አውቆሃልና። በቤቱ አምላክ እንደነበረ አውቋል። ከዛ በኋላ እንዳላወቀ መስሎ "ሳራ የት ናት?" አለው። አንተም. . .

አብርሀምም አለው፦ "ከበስተኋላህ፡ በድንኳን ውስጥ አለ. . . በድንኳን ውስጥ አለች" አለው።

አንተም ይሆን ያለውን ነገርካቸው፡ ይሁን እንጂ ሳራ በልቧስትጠራጠር፣ አብርሀምን እንዲህ አልከው፦ "ሳራ በልቧ ይህ አይሆንም ብላ ለምን ተጠራጠረች? ለጌታ የሚሳነው ነገር አለን?"

አምላክ ሆይ! የቃል የአምላክ መገለጥ የሆንክ ኢየሱስ፣"በሰዶም ዘመን እንደነበረ" የአህዛብ ዐለም በከባድ ጥፋት ከመጥፋቷ በፊት፡ የአህዛብ ሙላት ከመሆኑ በፊት፤ ዐለም፡ ሰዶማውያንእንደነበሩበት ዐይነት ሁኔታ ላይ ትዘፈቃለች ብለሃል። እንግዲህ አንተ እንዳልከው ይሄው ሶዶማዊነት ባለበት መሀል ነን! እንዲሁም በዛች ሰዐት የሰው ልጅ ማለትም "ነብዪው" እንዲገለጥ ተናግረሀል።አምላክ ሆይ ቃልህን ፈጽመው። እኛም አማኞች ልጆችህ፡ ለጸሎት ሰልፍ ስንሰለፍ ህዝቡ እምነት እንዲኖሮው፡ ኦ ጌታ ሆይ እምነት እንድትሰጠንልቦቻችንን ትሁት በመድረግ እንጠባበቅሀለን። አባት ሆይ የማምሻው ዘመን ነውና። የአምላክን ልጅ (የነበረው፣ ያለው፣ የሚመጣውን)የማምሻው ብርሃን፡ እራሱን በራሱ ትንቢት ይግለጽ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ አሜን።

73 እንግዲህ አሁን ለታመሙት ለመጸለይ ተዘጋጅቼአለሁ። ይህ ሁሉ ግንእንዴት እኛ በቆምንበት አሁን መሆኑ እንግዳ ነገር ነው፥ እንዲሁም ቆሜ ህዝቡን ሙግትን እሞግታለሁ፥ በዚሁም፥ ኣምላክ ኣምላክ ነውበማለቴ በመላ ኣገሪቱ ተጠምጃለሁ። ሊወድቅ አይችልም። እንዲሁም አደርገዋለሁ ብሎ ቃል የገባውን፥ ሳያደርግ አይቀርም፡

ምክንያቱአደርጋለሁ ብሎ ቃል ስለገባ። ስለዚ እሱ በተናገረው ሁሉ፥ ሙሉ ለሙሉ እተማመናለሁ። ስለዚ መምጣቱን እጠባበቃለሁ፥ “ባላሰባችሁትሰዐት” ዐለም ባላሰበችበት ሰዐት “እንደሚገለጥ” እሱ እንደተናገረ፥ በየትኛውም ሰዐት እንዲገለጥ እጠባበቀዋለሁ።

እንግዲህ፥ እስከማውቀው ድረስ . . . በራሴ ጉባኤ ውስጥእንዳለሁ አውቃለሁ፥ እንዲሁም በዚህ ከተቀመጡት ጥቂቶቹን አው - አውቃቸዋለሁ። ወንድማችን ራይት እና ጥቂት ከዚህ ከተቀመጡት መካከልአውቃቸዋለሁ። ይሁን እንጂ አብዛኞቻችሁ አላውቃችሁም። ጌታ በዚሁ ማታ ይሄን ያደርጋል ብየ የምልበት ምንም መንገድ የለኝም። ላለፉትአመታት እና አመታት ይሄን ሲያደርግ አይተነዋል፥ በዚሁ ምሽት ግንላያደርግ ይችላል። እኔ አላውቅም። እሱ ልኡል ነው። የእሱ ስራ ነው። ማድረግ የሚሻውን ያደርጋል። ማድረግ ያለበትን ማንም ኣይነግረውም።ፍቃዱን እና መንገዱን የሚጠብቅ ነው። ይሁን እንጂ፥ ቃል በገባውመሰረት እንዲያደርግልን እጠይቀዋለሁ። እኛን ለመጥቀም ስለሚያስፈልገን ሳይሆን ስለ እንግዶቹ፥ መንፈስ ቅዱስ ይቀባቸው ዘንድ .. . አሁን እሱ . . . ምናልባትም ይቀባናል። እንግዲህ እኔን የፈለገውን ያህል ይቀባኝ፥ እናንተንም እንድታምኑ፡ በርግጥ ይቀባቿል።

74 እንግዲህ አሁን የጸሎት ሰልፍ እንዲኖረን፥ አቅሜ የቻለውንምያህል ለታመሙት መጸለይን እፈልጋለሁ። ስለዚ፥ ሁለት ምርጫ አለን፥ አንደኛው፥ ህዝቡን ወደዚሁ ጠርተን ለጸሎት እንዲሰለፉ፥ አብረዉኝያሉ አገልጋይ ወንድሞች አሉኝ፥ እነሱም ወደዚህ ጠርተን እጆች ጭነን እንጸልይላችኋለን። ወይም ደግሞ፥ ለእናንተ ሁሉን ማድረግ የሚቻለውእሱ ስለሆነ የጌታን ስም እንጠራለን፥ የእኔ እጆች፥ እንደእናንተ እጆች የሰው እጆች ናቸው። ነገር ግን ቅሉ፥ ይሄን የሚያደርግየሰው እጅ አይደለም፡ ነገር ግን የጌታ ቃል ነው። ይህን የሚያደርገው፥ በቃሉላይ ያለ እምነት ነው። ሳይንሳዊ ነገር የለበትም፥ሙሉ ለሙሉ ኢ-ሳይንሳዊ ነው።

ክርስትያን ሆኖ፥ በጦር ዕቃው ላይ አንዳች ሳይንሳዊ ነገርያለው ሰው የለም። ይሄን ታውቃላችሁ? ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ብዙ-መቻል፥ መልካምነት፥ ትህትና፥ ጨዋነት፥ ትዕግስት፥ እምነት፥መንፈስቅዱስ እነኚህ ሁሉ፥ በሳይንስ ዕይታ የማይታዩ ናቸው። እውነት እና ዘለአለማዊ የሆነውም ይህ ነው። ከመሬት ሲመጣ ያያችሁትሁሉ፥ በመሬት ይጠፋል። በአይናችሁ ሳታዩት እንዳያችሁ የምታውጁት ነገር ሁሉ ግን፥ ከማይታይ ዘለአለማዊ ዐለም ነው።

75 ጌታ ከዚህ መልዕክት በኋላ፥ ያኔ መጀመርያ ያደረገውን ነገርአሁንም እያደረገ፥ ራሱን እየገለጸ አሁን እዚሁ ከገለጸ፥ ታምኑታላችሁ? እንደ ፈውሳችሁ አድርጋችሁ ትቀበላላችሁ? ጌታ ያድርግልን።አሁን፥ በዚህ ቤት ያላችሁ ሁላችሁ፥ ማን እንደሆናችሁ፣ ከወዴት እንደመጣችሁ አንጨነቅበትም፥ ይሄንን መልእክት እውነት እንደሆነበእርጋታ እንድታምኑት እጠይቃችሁኋለሁ። አምላክ ለዚህ ሰዐት፥ በመጽሓፍ ቅዱሱ ያለውን መልዕክት፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ህያው ሆኖ በዚህስፍራ መኖሩን ነው። አሁን በቅርበት . . .

እናንተ ሁላችሁ እንደምታውቁኝ፥ ይሄው እኔ በዚሁ ባደግኩባትከተማ ውስጥ ነኝ። ትክክለኛ የስዋስው ትምህርት እንኳን የለኝም። ይህ ሁሉ እውነት ነው። ለረጅም ጊዜ አውቃችሁኛል፥ ቅን እና ትሁትመሆኔን ለማሳየት በእናንተ ፊት በቅንነት እና በትህትና መኖሬን ተስፋ አደርጋለሁ። ግብዝ ሰው አይደለሁም። ነቀፌታዎቼም ቢሆኑ፡እንደዛ ነህ አይሉም። ብቻ “አንተ - አንተ ግብዝ አይደለህም፥ ይሁን እንጂ እንዲሁ መሀይም ነህ። ያለ ፈቃድህ በጭፍን የተሳሳትክነህ።” ይላሉ። እኔ ግን በጭፍን የተሳሳትኩ አይመስለኝም፥ ምክንያቱ የጌታ ቃል ራሱ ስለመልዕክቴ ይመሰክራልና፥ ማን እንደሆነምሊነግራችሁ ያስፈልጋል። እኔ አይደለሁም ብየ ስናገር በግልጽ ሰምታችሁኛል፥ ስለዚህ እሱ ነው። ትክክል ነው? እንግዲህ በጌታ እምነትንያዙ። ጌታን ካመናችሁት፥ እሱ ያደርግላቿል። ድሮም እንዳደረገ፥ አሁንም ካደረገ፥ እግዲህ እሱ አምላክ ነው። ታምናላችሁ?

76 ታምናላችሁ? እዚህ ከፊቴ የተቀመጠች ሴት፥ ከልቧ እየተመለከተችኝአይኖቿ እምባ አቅርሯል። ማን መሆንዋን አላውቅም፥ በፍጹም አይቻት አላውቅም። እኔ ላንቺ እንግዳ ነኝ። አምላክ የልብሽን ሚስጢር፣መሻትሽ፣ ሐጢአትሽ ወይም የሆነ ይሁን ያውቃል ብለሽ ታስቢያለሽ? እንደሚያውቅ ታውቂያለሽ? ያደረግሽውን፥ ያላደረግሽውን ወይም መሻትሽእና ሐጢአትሽን፥ ምንም ይሁን እንደሚገልጽልኝ ታስቢያለሽ? እንግዲህ እንደዛስ ቢያደርግ፥ እንድታምኚው ያደርግሻል ወይ? እሱ መሆኑንእንድታውቂው ያደርግሻል ወይ? እሱ እንደሆነ አድርገሽ ትቀበዪዋለሽ? አሁን የሚያስጨንቅሽ ሐጢአትሽ አይደለም፥ ምክንያቱም ንስሐገብተሻልና። አሁን የምትጠሚው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ትቀበያለሽ። በዙርያዋ ሲንቀሳቀስ አይቼዋለሁ።

ምናልባት እናንተ ሴትየዋን እያየኋት እንደነበር እንድታውቁ፥እያየቺኝ እንደነበር፥ መንፈስ ቅዱስን እንዳሳያችሁ እፈልጋለሁ። ወደዚህ እዚ ከእግሬ ስር የተቀመጠችውን ትንሽየ ሴት ላይ ተመልከቷት።እንዲህ ስል እሷም የምትፈልገው ይህ ነው፥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው የምትፈልገው። የኔ እህት፥ እንደምትቀበዪ ታምኚያለሽ? እቺንሴት ከዚህ በፊት በፍጹም አይቻት አላውቅም፥ እጅሽን ከፍ አድርጊ።

77 ራሱን ዝቅ አድርጎ፥ እዛ ማዶ የተቀመጠውን ኮሌታው የተዛባበት ሰውየ እዩት። በፊኛ በሽታ የምትሰቃይ ሰው ነህ። አምላክ እንደሚፈውስህ ታምናለህ? ከተቀበልክ፥ እጅህን ወደላይ ከፍ አድርግ። መልካም፥ጌታ መሻትህን ይፈጽምልህ።

እዚህ ቁጭ ብሎ ያለውን ወጣት፥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትንይናፍቃል። ነጭ የክር ከረባትህን ወደኋላ የሰቀልክ እዛጋ፥ ጌታ እንደሚሰጥህ ታምናለህ? አምላክ ይፈጽመዋል።

የዚህን ሰው ጸሎት ደግሞ ስለ ሚስቱ ነው፡ ሚስቱ በአንድተቋም ውስጥ ናት ያለችው። ጌታ እንደሚፈውሳት፣ እንደሚያድናት ታምናለህ? አመንከው? ውሰድ ተቀበል።

አንተኛው እጅህን በጉሮሮህ ላይ ያደረግ፥ እያስጨነቀህ ያለውንየልብ በሽታን እና ያለህን የሆድ ህመም ጌታ እንደሚፈውስህ ታምናለህ? አሁንም እዛ ሆነህ እየተሰቃየህ ነህ ያለህው። እውነት ነው?እንደፈወሰህ አመንክ? ፈውስህን ተቀበል። አሜን።

78 አያችሁ፥ ትላንትናም ዛሬም እስከ ለዘለአለም እርሱ ያውነው። እነዚህን ሰዎች የማውቃቸው እንደሆነ ለማወቅ ጠይቋቸው። እኔአላውቃቸውም። እሱ ግን ያውቃቸዋል። አሜን። እዛ በግድግዳው ማዶ ላይ በበራው መብራት ስር የተቀመጠውን ሰውየ ተመልከቱት። በጀርባአጥንት ህመም እየተሰቃየ ይገኛል። የዚህ አገር ሰው አይደለም፥ ከጆርጂያነው። አቶ ዱንከን፥ በሙሉ ልብህ እመነው፡ ጌታ የጀርባህን ህመም ይፈውሳል። በሙሉ ልብህ ታምናለህ? ጌታ ይባርክህ።

እዛጋ ከኋላ ተቀምጦ እኔን እኔን እያየኝ፥ በጀርባ ህመምየተያዘ፥ ይሄው እዛጋ አለ። እኔ አላውቀውም፡ ነገር ግን አቶ ቶምፕሰን ነው። ታምናለህ? እዛጋ ማዶ ተነሳ፥ እኔ ላንተ እንግዳእንደሆንኩ . . . ። ትክክል ነው። አንተ ግን ተቀምጠህ እየጸለይክ ነህ። የጀርባህ ችግር አሁን ተፈውሰሃል። ኢየሱስ ክርስቶስፈውሶሃል።

79 "አመሻሹ ላይ ብርሀን ይሆናል።" አይታያችሁም ወይ፣ ዛሬማታም እዚ ነው! ታላቁ እኔ ነኝ እሱ ነው። ትላንትናም ዛሬም እስከለዘለአለም ያው ነው። ታምናላችሁ? ራሱን እያስተዋወቀና፥ማንነቱን በትንቢት እየለየ ያለው፡ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን አረጋገጣችሁ፣ አምናችሁ ረካችሁ?

ስለ አይን አትጨነቁ። ጌታ የታመመንና የተጠቃን ይፈውሳል።

እዚ ካላችሁ ሰዎች . . . የታመማችሁ ስንቶቻችሁ ናችሁ?እስኪ እጆቻችሁን እንየው። ጠንከር ያለ መሻት እና ስህበት ያለ ይመስላል። ከእናንተ መካከል ምናልባት የጸሎት ካርድ ያላችሁ ሰዎችትኖራላችሁ? እዚህ እንዴት እንደማገኛችሁ አላውቅም። ለእናንተ እንድጸልይ እፈልጋለሁ እንዴት እንደማደርግ ግን አላውቅም። ምን እንደሆነአያችሁ፡ ወደ ግንቡ ተመልከቱ፥ ወደ አሉበት እንዴት ላልፍ እችላለሁ? አንደኛው መተላለፍያ ቢጨናነቅባችሁ ሌላኛው ቢዘጋባችሁስ?ሁሉም ሰው ባለበት ይሁን።

80 አድምጡ፣ እኔን ስሙኝ። በጌታ ስም ነግሬአችሁ ከሚፈጸምውጪ ነግሬአችሁ የማውቅ ነገር አለ? ትክክል ነው? ሁልጊዜ ሁሉም ነገር ትክክል ነበረ። በህይወቴ ሰባራ ሳንቲም ስጡኝ ብየ አልጠየቅኋችሁም።ጠይቄ አውቃለሁ? አንድም ቀን አልጠየቅኩም። በህይወቴ ምጽዋት ተቀብየ አላውቅም። እዚ ገንዘብ ፍለጋ አልመጣሁም፣ እናንተንም ለማታለልአልመጣሁም። እዚ ያለሁት፥ የዘመኑን የአምላክን ቃል ለእናንተ ለመግለጥ ነው። እውነትን ነገርኳችሁ፥ ጌታም ያንን እውነት እንደሆነመስክሮአል። እንግዲህ አሁን ቅዱስ ቃላት እንዲህ ይላሉ ብየ እላቹኋለሁ፥ ኢየሱስ እንዳለ አማኞች እጆቻቸውን በበሽተኞች ላይ ቢጭኑ"በሽተኞቹ ይፈወሳሉ!" ብሏል። ታምኑታላችሁ? እንግዲህ በጌታ መገኘት፥ አሁን እንደሚያደርገው አታምኑምን?

81 አሁን እጆቻችሁን አንዳችሁ ባንዳችሁ ላይ ጫኑ፥ ለጥቂትደቂቃዎች ጫኑ። አሁን፡ አትጸ - አትጸልዩ ብቻ እጆቻችሁን ተጫጫኑ በምድሪቱ ያላችሁም ሁላችሁ እንዲሁ አድርጉ። እኔም፥ እኔ ራሴበእነዚህ መሃረቦች ላይ እጄን እጭናለሁ። ለአንድ ደቂቃ እንድትመለከቱኝ እፈልጋለሁ። ጌታ ሳይፈጽመው የቀረ ነገር ምን አለ? እንግዲህኢየሱስ ማንነቱን በትንቢት ይለያል ብለን ያነበብነውን እና የነገርናችሁ ትንቢትን ተመልከቱት። እንዲሁም ዘመኑን እና በዚህ በምኖርበትዘመን ላይ ናቸው ብለን ያስቀመጥናቸውን ያለፉት ሶስቱን ሳምንታት አስተውሉአቸው። ያነበብነውን አስተውሉት፥ ሀሰተኞች ነብያቶች እናየተመረጡትን ለማታለል የሚባልላቸውን ምልክቶቹንስ። ቃሉ እንዴት እንደተገለጠ፣ የዚህ ዐለም አምላክ፣ ውሸት የሰዎችን ልብ እንዴትእንዳሳወረ። እንዲሁም ደግሞ ጌታ ራሱ በትንቢቶቹ፥ እነዚህ ነገሮች ሁሉ በሎዶቅያ ዘመን እንደሚፈጸሙ መናገሩ። ያልተፈጸመ ነገርየለም። አምላክ አሁንም እዚህ ነው፡ ያ ከትንቢቶች ተነስቶ ለኤማሁስ ሰዎች ማንነቱን የተረከላቸው ራሱ አምላክ፥ በዚህ ምሽትም ለዚህትውልድ በተነገሩ ትንቢቶች የመገኘቱ ማንነት እያሳየ እዚሁ አለ። ትላንትናም ዛሬም እስከለዘለአለም ያው ነው። ታምናላችሁ? እንግዲህእጆቻችሁ አንዳችሁ ባንዳችሁ ላይ ጫኑ። ለራሳችሁ እንዳትጸልዩ፡ እጃችሁን ለጫናችሁበት ሰው ጸልዩ፥ እሱም ለእናንተ ይጸልያልና።አስተውሉ፥ እንዳትጠራጠሩ።

82 አሁንም፡ እኔ የማይበትን አቅጣጫ ካያችሁ! በዚህም ስፍራላይ ቆሜ እናንተን እንደማልዋሻችሁ ካወቃችሁ። ከገባችሁ እና፣ እምነታችሁምበአየር - በአየር ላይ የሚሄደውን የከበረውን፣ ሳይንስ ፎቶ ያነሳውን፣ የሚያርፍበት መልህቅ የሚሆንለትን ስፍራ ፈልጎ፥ በዚህ ህንጻየሚያንዣብብ መንፈስ ቅዱስን ወደ እናንተ መማረክን ብትችሉ። እመን ብቻ ወንድሜ። በቅዱስ ቃል እና በሌሎች ሁሉ ገልጾታል። እውነትነው። እንግዲህ አሁን፥ እጆቻችሁ በጫናችሁበት ሰው በትህትና ጸልዩ፥ እነሱም ለእናንተ ይጸልዩ።

83 የተወደድክ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ "ሁለት ወይም ሶስት ሆናችሁበስሜ በምትሰባሰቡበት ስፍራ በመካከላችሁ እገኛለሁ። የሚያምኑትም እነዚህን ምልክቶች ይከተሏቸዋል፥ እጆቻቸውን በታመሙት ላይ ቢጭኑ፡ህመምተኞቹ ይፈወሳሉ" ባልከው ቃል እና በሰጠህን ተስፋ፥ ጌታ ሆይ እዚህ መሆንህን አውቀናል። እንዲሁም፡ ታላቁ መንፈስ ቅዱስ በስልክመስመር ውስጥ ወዳሉት ጉባኤዎች ሁሉ ይድረስ። አሁን በዚ ሰዐት በዚች ቤተክርስትያን እያየነው ያለውን ቅዱስ ብርሀን፡ በእያንዳንዳቸውላይ ይረፍ፥ እንዲሁም በዚህ ሰዐት ከደዌአቸው ይፈወሱ። ጠላት ዲያብያብሎስን በክርስቶስ መገኘት ሆነን እንገስጻዋለን፥ የጠላታችንዲያብሎስ መሸነፍ የምናውጀው - ስለኛ በተሰቃየው፥ በጌታ በኢየሱስ ሞት እና በሶስተኛውም ቀን ድልን በማድረግ በተነሳው፥ ከአስራዘጠኝ መቶ ዐመታት በኋላ ዛሬ ህያው ሆኖ ዛሬ ማታ በመካከላችን መሆኑን በማረጋገጥ ነው። እንዲሁም የህያው የአምላክ መንፈስ፥ የሁሉንምልብ በእምነት እና በሀይል፣ እንዲሁም በዚ ሰዐት በዚች ቤተክርስትያን ውስጥ እየተሽከረከረ ባለው ብርሃን መገኘቱን በሚያስታውቅ፥በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ የተነሳ፥ ፍቅርን እና ፈውስን ለሁሉ ይሁን። ለአምላክ ክብር በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አድርግ።

እነኚህ የጸለይንባቸው መሀረቦች፥ ሊደርሳቸው ለተገባቸውታማሚዎች እና ተጠቂዎች ይድረሱ። አሁን እዚሁ ያለው መንፈስቅዱስ ራሱን ያሳይ፥ እነኚህ በሚያርፍባቸው ታማሚዎች ላይ ራሱን ያሳይ።የአካላቸው በሽታ እስኪፈወስ ድረስ የአምላክ መገኘት በልባቸው እምነትን ይሙላባቸው። እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ባርያዎች፥ ይህ ሁሉለጌታ ክብር፥ በኢየሱስ ክርስቶስ መገኘት እንዲሁም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ጠየቅን። አሜን።

84 አሁን ከልባችሁ፥ ችግሮቻችሁ ምን ይሁን ምን አይገደኝም፥የጌታ ቃል የለመናችሁትን ሁሉ እንዳደረገላችሁ ከልባችሁ ታምናላችሁ? [ጉባኤው ሁሉ "አሜን" በማለት - መለሱ።] እንደሚታየኝ እጆችሁሉ እንደተነሱ አምናለሁ። ካመናችሁት፥ ሁሉንም መፈጸሙን አስቡ።

እናንተ፡ አገልጋዮቻችሁ እና ወዳጆቻችሁ እጆቻቸውን ጭነውባችሁ፥በስልክ መስመሮች ያላችሁ ሁሉ፥ በሙሉ ልባችሁ መፈጸሙን ካመናችሁ፥ ተፈጽሟል። በዚህ ምሽት ህያሉ መንፈስ ቅዱስ በዚህ ጉባኤ አለ።ትላንትናም ዛሬም እስከ ዘለአለም ያው መሆኑን ለማሳየት፥ የልብ ሚስጢር እያስታወቀ፣ የህልውናው ማንነት እያሳየ፣ ራሱን በዚ በግድግዳውጥግ በማሳየት፥ ወደዚህ እየመጣ፥በሕንጻው ላይ እየወጣ በህዝቡ ላይ ሲመላለስ አየዋለሁ። በመካከላችን ነው! እሱ አምላክ ነው፥ ፈጽሞየማይወድቅ - አምላክ።

85 በተነሳው ኢየሱስ ክርስቶስ መገኘት መሆናችን ማወቃችንስበውስጣችን ልባችን ይነድብን አልነበረምን፥ አሁንስ ይነድብን የለምን፥ የህያሉ ጆሆቫ የምስሉ መገለጫ ለሆነው፥ የነብዩን አትኩሮትለመሳብ በሚነድ ቁጥቋጦ ላይ የወረደው የእሳቱን አምድ፥ ከሙሴ እና ከኢያሱ ሌላ ማንም ቢነካው እስኪገደል ድረስ በተራው ላይ የወረደው፥ለእርሱ ለዘለአለም ክብርና ምስጋና ይድረሰው። በዚህ ጊዜ ተጠርቶ እንደወጣ ህዝብ ምሳሌ ይሆኑ ዘንድ፥የእስራኤልን ልጆች በበረሀውጉዟቸው የመራቸው እንዴት ነበር። እነሆ እሱ፥ በሳይንሳዊ ምርምር፥ ከሳይንስም በፊት ራሱን አሳውቆአል። ትላንትናና ዛሬ እስከ ለዘለአለምያው መሆኑን ለማሳየት፥ በዚ ዘመን ያደርጋቸው ዘንድ የተነገሩ ትንቢቶች፥ ድርጊቶቹ እና ትንቢቶቹ፥ ትክክለኛ ማረጋገጫ ናቸው። በውስጣችንልባችንን እንዲያቀጣጥል ይህ በቂያችን አይደለምን? ጌታ ይባርካችሁ።

86 አሁን፡ ሁላችንም አንድላይ ተነስተን፥ ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኜ እና ፈዋሼ አድርጌ አሁን እቀበለዋለሁ እንበል። [ጉባኤው ሁሉ "ኢየሱስ ክርስቶስን እንደግል አዳኜ እና ፈዋሼ አድርጌ አሁን እቀበለዋለሁ" አለ።] በጸጋውም ["በጸጋውም፣"] ከዚች ሰዐት ጀምሮ ["ከዚች ሰዐት ጀምሮ"] አምላክ ሆይ["አምላክ ሆይ"] በልቤ ውስጥ ["በልቤ ውስጥ"] አለማመን አይግባ ["አለማመን አይግባ፣"] የዚህን ዘመን ["የዚህን ዘመን"]ትንቢት ["ትንቢት"] ፈጽሜአለሁና። ["ፈጽሜአለሁና።"] ኢየሱስ ክርስቶስ ["ኢየሱስ ክርስቶስ"] ህያው መሆኑን እና ["ህያውመሆኑንና፣"] አሁንም ["አሁንም"] ወቅታዊው ቃሉን ["ወቅታዊው ቃሉን"] እያረጋገጠ መሆኑን ["እያረጋገጠ መሆኑን፣"] አምናለሁ። ["አምናለሁ።"] ስለሱ የተጻፉት ["ስለሱ የተጻፉት"] ትንቢቶችን፥ ["ትንቢቶችን፥"] አሁን በመካከላችን ተፈጽመዋል። ["አሁንበመካከላችን ተፈጽመዋል።"] እሱ አዳኜ ነው፣ ["እሱ አዳኜ ነው፣"] አምላኬ፣ ["አምላኬ፣"] ንጉሴ፣ ["ንጉሴ፣"] ሁሉ - በሁሉ- ነገሬ ነው። ["ሁሉ - በሁሉ - ነገሬ ነው።"]

87 የተወደድክ አምላክ ሆይ፡ ምስክርነታችንን ስማው። የህይወትንምእንጀራ በየእለቱ ስጠን። እኛም አምላክ ሆይ፥ ከጥልቅ ልባችን ምስጋናንእናናቀርባለን። ለአንተ ለታላቁ፥ የነብያት ሁሉ አምላክ፥ ክብርን እንሰጥሀለን። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

ኦ፥ እንዴት ያለ ድንቅ ወቅት፣ ድንቅ ጊዜ።

. . . እመን ብቻ

እመን ብቻ፥ በቃ እመን ብቻ

ነገር ሁሉ ይቻላል፥ እመን ብቻ።

እስኪ እንዲህ እንዘምረው።

አሁን አመንኩኝ፥ ኦ አሁን አምኛለሁ

ነገር ሁሉ ይቻላል፥ አሁን አምኛለሁ

አሁን አመንኩኝ፥ ኦ አሁን አምኛለሁ

ነገር ሁሉ ይቻላል፥ አሁን አምኛለሁ።

የናንተስ ምስክርነታችሁ ነውን? [ጉባኤው ሁሉ "አሜን"በማለት መለሱ።] እንግዲህ አሁን ራሶቻችን ዝቅ እያደረግን።

እስክንገናኝ! እስክንገናኝ!

በኢየሱስ እግር ስር፥ እስክንገናኝ፥

እስክንገናኝ! እስክንገናኝ!

ጌታ አብሯችሁ ይሁን፥ እስክንገናኝ!

[ወንድም ብራንሀም ጌታ ከናንተ ጋር ይሁን እያለ አንጎራጎረ።ከዛ በኋላ ወንድም ነቪለን "የምትለው ነገር አለህ?" አለው] ሊ ቫይል . . .

በኢየሱስ እግር ስር፥ . . .

እስክንገናኝ! እስክንገናኝ!

ጌታ አብሯችሁ ይሁን፥ እስክንገናኝ!

88 ራሶቻችን ዝቅ እንዳለ፥ ወንድማችን ሊ ቨይል፥በጸሎት እንዲዘጋልንእዚሁ ቆሞዋል። ወንድማችን ሊ ቨይል በዚሁ ጉባኤ ውስጥ፥ የተለያዩ ስነጽሁፎችን እና መጻሕፍቶችን የሚጽፍ ወንድም ነው። በብዙ ዘመቻዎች አብሮኝ ነበር፥ በጣም ድንቅ ነው። ሁሉም አገልጋዮችእዚህ መጥተው ባገኛቸው እና ብናገራቸው ደስ ባለኝ ነበር። የእውነቴን ነኝ፥

ገባችሁ። ሁላችሁም አገልጋዮች እናንተን እዚ በመቀበላችንደስተኞች ነን። እንዲሁም ከተለያዩ አብያተ ክርስትያናት የመጣችሁ ሁላችሁ ምእመናን፥ ስለመጣችሁ ደስተኞች ነን። “ጌታ አብሯችሁይሁን፥ እስክንገናኝ!” ማለታችንም እውነተኛ ጸሎታችን ነው። እጆቻችን ከፍ በማድረግ ራሶቻችንን ዝቅ ብለው፥ ደግመን በእውነት እናበጣፋጭ

ዝማሬ ለጌታ እንዘምር።

እስክንገናኝ! እስክንገናኝ!

በኢየሱስ እግር ስር፥ እስክንገናኝ፥

እስክንገናኝ! እስክንገናኝ!

ጌታ አብሯችሁ ይሁን፥ እስክንገናኝ!

www.messagehub.info

ስብከት በ
William Marrion Branham
"... ድምጹም በሚሰማበት ዘመን ..." ራእይ 10፥7